# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 164 የካቲት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# «ሰላምና ልማትን አምጥቶ በፍቅር ከመኖር ውጪ ሌላ ፍላጎት የለንም»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አቅም በፈቀደ መጠን ሰላምና ልማትን አምጥተን በፍቅር ከመኖር ውጪ የተለየ አጀንዳና ፍላጎት የለንም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከአማራ ክልል ሁሉም ዞኖች ከተውጣጡ ተወካዮች ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡

በውይይቱ ወቅት ለተነሱላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ማብራሪያ፤ አማራ ክልል ገና ከውጊያ ወጥቶ ዓመት እንኳን ሳይሞላው መኪናና አምቡላንስ ማቃጠል ትክክል እንዳልሆነና፤ ሃሳቦች ካሉ በውይይት ተነጋግሮ የሚቻለው ምላሽ ተሰጥቶበት፣ የማይቻለው ላይ ደግሞ በይቅርታ ማለፍ እንጂ መገዳደል እንደማያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

«አቅም በፈቀደ መጠን ሰላምና ልማትን አምጥተን ከእናንተ ጋር በፍቅር መኖር ብቻ ነው የምንፈልገው፡፡ ከዚህ የተለየ አጀንዳና ፍላጎት የለንም» በማለት ተናግረዋል፡፡

ለአማራ ክልል ትራክተር እንጂ ጥይት አያስፈልግም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለክልሉ ሰላም ተደጋጋሚ ጥሪ መቅረቡን ጠቅሰዋል፡፡

በሰላማዊ መንገድ ገብቶ መነጋገር የሚፈልግ ሰው መነጋገር መቻል እንዳለበትም አስታውቀዋል፡፡

«ሰላምና ልማትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









## ስተገልጋይ
### ክብር የነፈገው ተቋም

ገጽ 4



ዶክተር ኢሳ ካይድ መሐሙድ

## የኢትዮጵያ እና የሶማሊላንድ የባሕር በር ስምምነት በሦስተኛ አካላት አይቀየርም

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ እና የሶማሊላንድ የባሕር በር ስምምነት በሦስተኛ አካላት ተጽእኖ ሊቀየር እንደማይችል የሶማሊላንድ የውጭ ጉዳይና ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ዶክተር ኢሳ ካይድ መሐሙድ ገለጹ።

የኢትዮጵያ እና የሶማሊላንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያና ኬንያ
## በሰባት አዳዲስ የትብብር መስኮች በጋራ ለመሥራት ተስማሙ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ኬንያ ያላቸውን ታሪካዊ ግንኙነት ለማጠናከር በሰባት አዳዲስ የትብብር መስኮች በጋራ ለመሥራት በ36ኛው የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ስምምነት መፈራረማቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ከየካቲት 11 ጀምሮ እስከ 13 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ አካሂዷል፡፡

ከስምምነቱ በኋላ በጋራ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ እንደገለጹት፣ 36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ውጤታማ ነው፡፡ በኮቪድ 19 እና በሌሎች ምክንያት ላለፉት ሰባት ዓመታት አለማካሄዱን ገልጸዋል፡፡

ከሦስት ቀን ተከታታይ ስብሰባ በኋላ የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ በቋሚነት እንዲካሄድ ተስማምተናል፡፡ በስብሰባው ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ኬንያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ







# በመዲናዋ የአካባቢ ብክለት ያደረሱ ከአንድ ሺ በላይ ተቋማት ላይ ርምጃ ተወሰደ

## - 25 ጭፈራ ቤቶች ታሽገዋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ስድስት ወራት አካባቢ ላይ ብክለት ያደረሱ ከአንድ ሺ በላይ ተቋማት ላይ ርምጃ መውሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡ የማኅበረሰቡን የእረፍት ጊዜ ያወኩ 25 ጭፈራ ቤቶች መታሸጋቸውም ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ድዳ ዲሪባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ወራት በአካባቢ ብክለት ላይ በተደረገ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ አንድ ሺ 221 አገልግሎት ሰጪና አምራች ተቋማት ላይ የማስተካከያ ርምጃ ተወስዷል፡፡



አቶ ድዳ ዲሪባ

እንደ አቶ ድዳ ገለጻ፤ ርምጃ ከተወሰደባቸው ውስጥ አብዛኛው በአካባቢ ላይ የደምጽ ብክለት ያስከተሉ ሆቴሎችና ጭፈራ ቤቶች ናቸው ብለዋል፡፡

ርምጃው ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ማሸግ የሚደርስ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ድዳ፤ ከቅጣቱ ጎን ለጎን የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት ወደ አገልግሎት የመመለሱ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በ4 ሺህ 530 አገልግሎት ሰጪና አምራች ተቋማት ላይ ክትትል ለማድረግ አቅዶ በ5 ሺ ተቋማት ላይ ባለሞያ በመመደብ ክትትል ማድረግ መቻሉን አመልክተዋል፡፡

ባለሥልጣኑ በበጀት ዓመቱ 10 ሺህ አገልግሎት ሰጪና አምራች ተቋማት ብክለት እንዳያደርሱ ክትትል ለማድረግ ማቀዱንና ከማኅበረሰቡ የሚቀርቡ የብክለት ይወገድልኝ አቤቱታ ምላሽ መስጠቱን አክለው ገልጸዋል፡፡

የማኅበረሰቡን የእረፍት ጊዜ ያወኩ 25 ጭፈራ ቤቶች መታሸጋቸውን ገልጸው፤ አገልግሎት ሰጪና አመራች ተቋማት ምርትና አገልግሎት ከማቅረብ ባሻገርም ሂደቱ በኅብረተሰቡ ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የተቀመጠውን መስፈርት አክብረው ሊሠሩ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ከአካባቢ ብክለት ጋር ተያይዞ ከማኅበረሰቡ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

በከተማዋ ያለው የአየር ጥራት ምን ላይ እንዳለና የአየር ብክለት መጠን በምን ያክል ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ የአየር ብክለት መለኪያ መሣሪያዎች መተከላቸው አስታውሰው፤ መሣሪያዎቹ በሚሰጡት መረጃ መሠረት ለችግሩ አፋጣኝ ምላሽ እየተሰጠ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በዋናነት የከተማውን አየር የሚበክሉት ከመኪና፣ ከኢንዱስትሪዎች፣ ከግለሰብና ከጋራ መኖሪያ ቤቶች እንዲሁም ከሆቴሎች የሚወጡ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻዎች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ለዜጎች ምቹ የመኖሪያ አካባቢን ለመፍጠር ባለሥልጣኑ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ ነው ያሉት አቶ ድዳ፤ ኅብረተሰቡ ለአካባቢ ጥበቃ ሥራ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግም እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡



# በሀላባ ከበጋ መስኖ ከ107 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

## - 105 የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ለአርሶ አደሮች ተከፋፍሏል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም የበጋ መስኖ ልማት ከ107 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የሀላባ ዞን ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡ 105 የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ለአርሶ አደሩ መከፋፈሉም ተገልጿል፡፡

የመምሪያው ኃላፊ አቶ ሃጂ ኑርዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አንደገለጹት፤ በዘንድሮው የምርት ዘመን በዞኑ ከሚለማው 671 ሄክታር መሬት ከ107 ሺ ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

የበጋ መስኖ ልማት ሥራው በሁለት ዙር የሚከናወን ነው ያሉት አቶ ሃጂ፤ በመጀመሪያ ዙር 571 ሄክታር እንዲሁም በሁለተኛ ዙር 100 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል ብለዋል።

በዞኑ 30 ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ እየለማ መሆኑን ጠቁመው፤ ከዚህም ከአንድ ሺህ ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በበጋ መስኖ ልማት በዋናነት ስንዴን ጨምሮ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎችና የጓሮ አትክልቶች በስፋት እየለሙ መሆኑን አስረድተዋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታት ለመስኖ ሥራ የሚውሉ 105 የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ለአርሶ አደሮች መከፋፈሉን አመልክተዋል፡፡

የበጋ መስኖ ልማት ሥራው በመካናይዜሽን የእርሻ መሣሪያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ኃላፊው አስረድተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የበጋ መስኖ ልማት ሳይሠራባቸው የቆዩ መሬቶችን ወደ መስኖ ልማት ሥራ ማስገባት መቻሉን ጠቁመው፤ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ጥሩ መሻሻሎች መኖሩን ጠቁመዋል፡፡

ውሃ አጠር ከሚባሉ አካባቢዎች አንዱ ሃላባ ዞን ነው ያሉት አቶ ሃጂ፤ ከተለያዩ ተፋሰሶች የሚገኘውን ውሃ በማጠራቀም ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

በዚህም አርሶ አደሮች በዓመት አንድ ጊዜ ከማምረት ወደ ሦስት ጊዜ ወደ ማምረት መሸጋገራቸውን አስታውቀው፤ ለወጣቱም በርካታ የሥራ ዕድል መፍጠር እንደተቻለ ጠቁመዋል።

የበጋ መስኖ ልማት የአርሶ አደሮች ኑሮ እንዲሻሻልና ገቢያቸው እንዲጨምር ማድረጉን የጠቆሙት ኃላፊው፤ የበጋ መስኖ ልማት ሥራው ውጤታማ እንዲሆን በልዩ ትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

ሥራው በሚፈለገው መጠን ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግም ከተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ እንደሆነም አስታውቀዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በስንዴ ሰብል ላይ ጉዳት እያደረሰ ያለውን የግሪሳ ወፍ ለመከላከል ከአርሶ አደሩ ጋር በመተባበር እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

# በሀገራዊ ምክክሩ አጀንዳ

## አሰባሰብ የሚሳተፉ አካላት ማኅበረሰቡን በትክክል የሚወክሉ መሆን እንዳለባቸው ተጠቆመ

### - በአማራ ክልል ከኮሚሽኑ ጋር ለሚሠሩ መምህራን ሥልጠና ተሰጥቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዳማ፡- በሀገራዊ ምክክሩ የአጀንዳ ማሰባሰብና የምክክር ሂደት ላይ የሚሳተፉ አካላት ማኅበረሰቡን በትክክል የሚወክሉ መሆን እንዳለባቸው የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ። በአማራ ክልል ከኮሚሽኑ ጋር ለሚሠሩ የዩኒቨርሲቲ መምህራን ሥልጠና ተሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኦሮሚያ ክልል በወረዳ ደረጃ የአጀንዳ ሃሳቦችን ለማሰባሰብ ድምፅ የሚሰጡ የተሳታፊ ልየታ ሥራ ትናንት ተጀምሯል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባዬ ኦጋቶ (ዶ/ር) በወቅቱ ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተባባሪ አካላት ሥልጠና፣ የተሳታፊ ልየታ፣ የአጀንዳ ማሰባሰብ፣ በምክክር ሂደቱ የሚሳተፉ አካላትን የመለየት እና ሌሎች ሥራዎችን እየሠራ ነው።

ኮሚሽኑ በኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ ሸዋ ዞን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ወክለው የአጀንዳ ሃሳቦችን ለማሰባሰብ ድምፅ የሚሰጡ እና በምክክር ሂደቱ የሚሳተፉ ተወካዮችን ልየታ መጀመሩን ገልጸው፤ በዚህም ከሰባት ወረዳዎች የተውጣጡ ከ600 በላይ ተሳታፊዎች ወረዳዎቻቸውን እና የማኅበረሰብ ክፍሎቻቸውን ወክለው በአጀንዳ ማሰባሰብ እና በምክክር ሂደቱ የሚሳተፉ ተወካዮቻቸውን መምረጣቸውን አስታውቀዋል።

ከፋንታሌ፣ ሞጆ፣ ሎሜ፣ ቦራ፣ ቦሰት፣ አድአ እና ሊቨን ጩቃላ ወረዳዎች የተውጣጡ ተሳታፊዎች ተወካዮቻቸውን የመረጡ ሲሆን፤ ተሳታፊዎች ለአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ይወክሉናል የሚሏቸውን ሁለት ሁለት ግለሰቦችን ከአንድ ተጠባባቂ ጋር በየወረዳቸው እና በየማኅበረሰብ ክፍሎቻቸው መርጠዋል ብለዋል።

ተሳታፊዎቹ ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከአርሶ አደሮች፣ ከአባ ገዳዎች፣ ከነጋዴው እና ከሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ሲሆን፤ ስለሀገራዊ ምክክሩ አስፈላጊነት፣ ስለተሳታፊዎች ሚና፣ ኮሚሽኑ እስካሁን ስላከናወናቸው ተግባራት፣ በቀጣይ የምክክር ሂደቶች፣ በድምፅ አሰጣጥ ሂደት መራጮች ሊከተሏቸው ስለሚገቡ ሕጎች እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ገለጻ እንደተደረገላቸው ተናግረዋል።

በቀጣይ በሌሎች ወረዳዎች እና በክልል ደረጃ ድምፅ የሚሰጡ የሕዝብ ወኪሎች የመምረጥ ሂደትን እንደሚያከናውኑ ገልጸው፤ በአጀንዳ ማሰባሰብ እና በምክክር ሂደቱ ላይ የሚወክሏቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎችን ሲመርጡ በጥንቃቄ ሊሆን እንደሚገባ አሳስበዋል።

ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በሀገር ጉዳይ ላይ የሚያግባቡ ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ሀገራዊ ኃላፊነት ወስዶ እየሰራ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ እስካሁን



አምባዬ ኦጋቶ (ዶ/ር)

ባለው ሂደት ከተበባሪ አካላት ስልጠና ጀምሮ የውይይት አጀንዳ ለመቅረጽ እና አካታች ሕዝባዊ ውይይት ለማካሄድ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎችን መስራቱን አመልክተዋል።

ምክክሩ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር ብሎም ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ያለመ በመሆኑ በአጀንዳ ማሰባሰብ፣ በምክክር ሂደቱና በሌሎች ስራዎች ላይ የሚወከሉት ተሳታፊዎች ማህበረሰቡንና አካባቢያቸውን በትክክል የሚወክሉና ሀሳባቸውን የሚያንጸባርቁ ሊሆኑ እንደሚገባ አስገንዘበዋል።

ሀገሪቱ ካለችበት ችግር ማውጣት የሚቻለው በመወያየት እና በመመካከር በመሆኑ ስኬታማ ምክክር ለማድረግ ሁሉም የድርሻውን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

መራጮች ድምፅ ሲሰጡ እያንዳንዱን ማኅበረሰብ ወክለው በክልል ደረጃ የሚሳተፉ እጩዎችን በጥንቃቄ ሊመርጡ ይገባል ብለዋል።

በሌላ በኩል በአማራና ትግራይ ክልሎች በነበረው የጸጥታ ሁኔታ የምክክር ሂደቱን ከሌሎች አካባቢዎች ጋር እኩል ማስኬድ እንዳልተቻለ ገልጸው፤ በአማራ ክልል የተሳታፊ ልየታን ለመጀመር ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር ለሚሰሩ ከ10 ዩኒቨርሲቲዎች ለተውጣጡ 26 መምህራን ስልጠና መሰጠቱን አብራርተዋል።

በሁለቱም ክልሎች የተባባሪ አካላትና የተሳታፊ ልየታን ጨምሮ ሌሎች ስራዎችን ለመስራት ከመንግስት የስራ ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ውይይት ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

በወረዳ ደረጃ ያለው የተሳታፊ ልየታ ስራ በሲዳማ፣ በአፋር እና በደቡብ ምዕራብ ክልሎች የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በደብዳቤ የሚጠሩት ተሳታፊዎች ደግሞ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሶማሊ እና በሌሎች ክልሎች መጠናቀቁን ገልጸዋል።

ዜና

# ‹‹ዮ ያ፤ ገዳፍ ጉጂን ናጌያ››

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

በጉጂ አባገዳዎች ዘንድ የሚፈፀመው 75ኛው የ‹‹ባሊ›› ሥልጣን ርክክብ መርሐ ግብር ትናንት በሚኤ ቦኮ ከጉብታማው ስፍራ አርዳ ጂላ ተከናውኗል። ጉብታው በአራቱም አቅጣጫ አካባቢውን ለመቃኘት ያስችላል። ለወራት ጠፍተው ድንገት ብቅ እንዳሉ እንደ ምሽት ከዋክብት በባህላዊ አልባሳት የደመቁ አባ ገዳዎች፣ ሀዳ በላዎች፣ ሃዳ ሲንቄዎች፣ ታዳጊዎች እና ታዳሚዎች የበዓሉ ድምቀት ናቸው።

አርዳ ጂላ ከአካባቢው ሥፍራ ሁሉ ጎላ ብሎ የሚታይ ሲሆን፤ በጠዋት ግዳጅ እንደቀናው አንበሳ ደረቱን ለፀሐይ መውጫ ሰጥቶ ለዕይታ ሰቅዞ የሚይዝ ማራኪ ተፈጥሮን የተላበሰ ነው። ጉብታማው ስፍራ ‹‹አርዳ ጂላ›› ደግሞ ብቻህን አትሁን የተባለ ይመስል ዙሪያውን ጥቅጥቅ ባለ ደን የተከበበ ሲሆን፤ በዘመድ አዝማድ ተከባ ወረቷን እንዳልጨረሰችና በፅኑ እንደምትጠበቅ አዲስ ሙሽራ ዙሪያው በጥቅጥቅ ደን ይጠበቃል። የአካባቢው ደን ጥብቅ በመሆኑ አርዳ ጂላ ውበቱ ሳይነጥፍ ዛሬም አለ። አርዳ ጂላ በጉጂ አባገዳዎች ዘንድ በየስምንት ዓመቱ የሚፈፀመው የ‹‹ባሊ›› ሥልጣን ርክክብ መርሐ ግብር የሚከናወንበት ስፍራ ሲሆን፤ በአካባቢው ማኅበረሰብም ሆነ በአባ ገዳዎች ዘንድ እንደ ቅዱስ ስፍራም ጭምር የሚቆጠር ነው።

በዚህ የበጋ ወቅት የአካባቢው አረንጓዴ መላበስ ምናልባትም ተፈጥሮ ለዚህ ሥፍራ በእጅጉ አድልቷል ለማለት ይዳዳል። ታዲያ የአካባቢው ማኅበረሰብ ለዚህ መርሐ ግብር ለወራት ሲዘጋጅ የነበረ ሲሆን ትናንት በተረጋጋ መንፈስ በማለዳው ከስፍራው ተገኝቶ መርሐ ግብሩን እየተከታተለ ነበር።

በሥልጣን ርክክቡ መሠረትም የሐርሙፋ አባገዳ ለሮበሌ አባገዳ ሥልጣን ያስረከበ ሲሆን፤ ቀደም ሲል የጉጂ አባገዳ የነበሩት አባገዳ ጂሎ ማንዶ አዲስ ለተሾሙትና ለሚቀጥሉት ስምንት ዓመታት ሥርዓቱን በዋናነት ለሚመሩት አባገዳ ጃርሶ ኡጎ ሥልጣን አስረከበዋል።

ሥልጣኑንም የተረከቡት አባ ገዳ ጃርሶ ኡጎ፤ ላለፉት 74 ዓመታት በየስምንት ዓመቱ አንዳችም ዝንፈት ሳይከሰት ርክክቡ ሲፈፀም መቆየቱን በማስታወስ



ፎቶ ገበቦ ገብሬ

አባ ገዳ ጃርሶ ዱጎ

አባቶቻችን ለእኛ ያቆዩትን ትውፊትና ሥርዓት እኛም ለቀጣይ ትውልድ ለማስመቀጥና ሕዝብን ለማገልገል አደራ የተቀበልንበት ቀን ነው ሲሉ በቀጣይ በብዙ መትጋት እንደሚጠበቅባቸው ይናገራሉ።

ገዳ ሰላም ነው፤ አባገዳዎች ደግሞ ሰላም፣ ልማትና አንድነትን ማምጣት ይጠበቅብናል። ለዚህም ከመንግሥት ጋር እንሠራለን፤ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎችም ‹‹ዮያ›› ‹እንኳን እኛ ለምንተጋለትና ለምንሳሳለት ሰላም እና አንድነት በደህና መጣችሁ› ብለዋል።

አባ ገዳዎች በኦሮሚያ ብሎም በሀገር ልማት እና ሰላም ቅድሚያ ሰጥተው እንደሚሠሩ የተናገሩት አባገዳ ጃርሶ ኡጎ፤ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያሉ አለመግባባቶችን በሰላም ለመፍታት ጥረት ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል። በተለይም ጦር መሣሪያ ያነገቡ አካላት በገዳ ሥርዓት መሠረት ለውይይትና ለሕዝብ ሰላም ወደቀያቸው እንዲመለሱ ጠይቀዋል። መንግሥትም በሆደ ሰፊነት ነገሮችን ይመልከት፤ ችግሮች በውይይት ይፈቱ፤ ለሕዝቡ ሰላም ይስሩ ብለዋል። ‹‹ዮያ፤ ገዳፍ ጉጂን ናጌያ›› ወይንም ‹‹ዮያ፤ ጉጂ እና ገዳ ሰላም ነው›› ሲሉ ስለ ሰላም አበክረው ጠይቀዋል።

የጉጂ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ነጋስ ቡላላ በበኩላቸው፤ የኦሮሞ ሕዝብ ዘመናትን የተሻገረ እና ቀጣይ ትውልድም ሲናገረውም ሆነ ሲኖረው የሚያኮራው ከዓለም ሥልጣኔ ቀድሞ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ህያው አድርጎ የነበረ እና ነገም በተምሳሌትነት የሚነሳለት ባህል ባለቤት ነው። በመሆኑም በገዳ ሥርዓት መሠረት የሚፈፀመው ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር የእውነተኛ ዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብም ሆነ ተግባር መሠረት በመሆኑ የጉጂ ዞን ለአባ ገዳዎች ትልቅ ክብር ይሰጣል፤ በጋራም ይሠራል ሲሉ ገልፀዋል።

በመርሐ ግብሩ ማጠናቀቂያ ላይ የተገኙት የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ፤ የገዳ ሥርዓት ሰላም የሚሰበክበትና የዴሞክራሲ ልምምድን ለዓለም ያስተዋወቅንበት ስለመሆኑ መታወቅ አለበት ይላሉ። ሥርዓቱ ብዙ ክፍለ ዘመናትን ተሻግሮ የመጣ ሲሆን ዓለም ለዛሬው ሥልጣኔ እንግዳ በሆነችበት ዘመን የኦሮሞ ሕዝብ ከራሱ አልፎ ለሌሎችም የሚተርፍ ባህል፣ እሴትና አንድነትን ይዞ ከትውልድ ትውልድ ሲያስተላልፍ የኖረ ነው። ይህም በመሆኑ የአሁኑ ትውልድ ታሪኩንና ወጉን በሚገባ የሚገነዘብበት ጥሩ ዕድል ተፈጥሮለታል። ይሁንና ይህ በቀላሉ የመጣ ሳይሆን ብዙ ዋጋ የተከፈለበት፤ በዘመናት ውስጥ ከባድ ፈተናዎችን የተሻገረ በመሆኑ ሁላችንም ልንንከባከበው ይገባል ብለዋል።

‹‹የኦሮሞ ሕዝብ የገዳ ሥርዓት በርቀት የሚመለከተው ሳይሆን ኖሮ በቅርበት የሚተግብረውና የሚያውቀው፤ የሚሰማው ብቻ በትምህርት ሥርዓት ጭምር ትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፈው የትምህርት ሥርዓት የተቀረፀለት ነው። በመሆኑም መንግሥት ለመሰል ሕዝባዊ ትውፊት ቅርሶች መጠበቅና መበልፀግ ብሎም በእጅጉ መመንደግ ከልብ እንደሚሠራ አረጋግጠዋል።



ፎቶ ሀዱሽ አብርሃ

አቶ ሄኖክ አህመድ

# ከ30 በላይ አዳዲስ ኩባንያዎች በአይሲቲ ዘርፍ ለመሰማራት ጥያቄ አቅርበዋል

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- ከ30 በላይ አዳዲስ ኩባንያዎች በአይ.ሲ.ቲ ልማት ዘርፍ ለመሰማራት ጥያቄ ማቅረባቸውንና አስሩ ሥራ ለመጀመር ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ አስታወቀ፡፡ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮችን ወደ ፓርኩ ለመሳብም የመሬትና የሕንፃ ኪራይ ሊዝ ዋጋ ማሻሻያ እያደረገ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

የፓርኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሄኖክ አህመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ፓርኩ እንደአዲስ ራሱን ችሎ እንዲቋቋም ከተደረገ ወዲህ ቁጥራቸው ከ30 የሚልቁ ኩባንያዎች በአይ.ሲ.ቲ ልማት ዘርፍ ለመሰማራት ጥያቄ አቅርበው አስሩ ወደ ልማት ለመግባት የሚያስችላቸውን ሥራ አጠናቀዋል፡፡

እንደእርሳቸው ማብራሪያ ፓርኩ በ2003 ዓ.ም ሲቋቋም በርካታ የአይሲቲ ኩባንያዎችንና ከ300 ሺ ለሚልቁ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታልሞ ቢሆንም በሀገር አቀፍና በተቋሙ የውስጥ ችግሮች ምክንያት እንደታሰበው ውጤታማ ሳይሆን ቆይቷል፡፡ በተለይም ሀገሪቱ በቴክኖሎጂ መስክ ወደከፍተኛ ደረጃ ያደርሳታል ተብሎ እንደታሰበው አስፈላጊ መሠረተ ልማትና ድጋፍ ያላገኘ በመሆኑ ስኬታማ ሥራ መሥራት አልቻለም፡፡

በዚህም ምክንያት በወቅቱ ገብተው ከነበሩት ድርጅቶች ውስጥም ከ60 በመቶ በላይ የሚሆኑት ጥለው የወጡበት ሁኔታ ተፈጥሮ እንደነበርና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 25 ብቻ በተጨባጭ ሥራ ላይ እንደነበሩ ዋና ሥራ አስፈፃሚው አመልክተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ግን መንግሥት ለዘርፉም ሆነ ለተቋሙ የተለየ ትኩረት መስጠቱን ተከትሎና ፓርኩ ራሱን ችሎ እንዲተዳደር በመደረጉ በርካታ ኩባንያዎች በዘርፉ ለማልማት ጥያቄ በማቅረብ ላይ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

‹‹አዳዲሶቹ አስር ድርጅቶች በሁለት ወር ጊዜ ሥራ እንደሚጀምሩ ይጠበቃል›› ያሉት አቶ ሄኖክ፤ በተለይ ከውጭ የሚገባውን ምርት በመተካት ሀገሪቱ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማዳንና አገልግሎትን በመሸጥ ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ የላቀ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ተብሎ እንደሚጠበቅ አስገንዝበዋል፡፡

በዚህ ረገድም ፓርኩ ባለሀብቶችን እንዲስብ፣ የቴክኖሎጂ አቅም በሀገር በቀል ድርጅቶች ለመጠቀም እንዲሁም የሥራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው የውጭና የሀገር ውስጥ ድርጅቶችና ግለሰቦች ወደ ፓርኩ ለማስገባት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ጠቁመዋል፡፡ አክለውም ፓርኩን በ2030 የአፍሪካ ዲጂታል ማዕከል ለማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራ እየተተገበረ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ለፓርኩ የመሠረተ ልማት ሳይሟላለት መቆየቱን፣ እንደኢንተርኔት፣ መብራት፣ ውሃ፣ ትራንስፖርት፤ የምግብ አገልግሎት በቅርበት አለመኖርና ለመሰል ችግሮች ተጋልጦ እንደነበርም አስታውሰዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ግን ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በመነጋገር እንደመብራት ያሉ መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ በማድረግ፤ የወጡትም ሆነ አዳዲስ ኩባንያዎች ወደ ፓርኩ ገብተው እንዲያለሙ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በሌላ በኩልም የሊዝ ዋጋ በጣም ከፍ ያለ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ማሻሻያ ተሰርቶ ወደ ቦርድ መላኩን ጠቁመዋል፡፡ ኩባንያዎቹ ማሻሻያው ጸድቆ ወደ ትግበራ እስኪገቡ ድረስ በነበረው አሠራር እንደሚቀጥሉ፤ ፀድቆ ወደ ትግበራ ሲገባ ደግሞ በተሻሻለው ተመን እንደሚሠሩ ውላቸው ላይ መካተቱንም ነው የገለጹት፡፡

በተጨማሪም ባለፉት ስድስት ወራት ፓርኩን በአዲስ መልክ የማደራጀት ሥራ ሲከናወን መቆየቱንና ችግሮቹን ለማስተካከል ጥረት መደረጉን ዋና ሥራ አስፈጻሚው አመልክተዋል፡፡



# በሙዚቃው የተለያዩ ትውልዶችን ያስተሳሰረው ጌታቸው ካሳ አረፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ‘ህገሬን አትንኳት’፣ ‘አዲስ አበባ’ እና ‘ትዝታ’ በተሰኙ ሙዚቃዎቹ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያተረፈው አንጋፋው ሙዚቀኛ ጌታቸው ካሳ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ሙዚቀኛው ባደረበት ሕመም በየካቲት 12 ሆስፒታል በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ የካቲት 12 ቀን 2016 ዓ.ም ሌሊት ሕይወቱ አልፏል። በሙዚቃው የተለያዩ ትውልዶችን ማስተሳሰር የቻለው ጌታቸው ካሳ በኢትዮጵያ ሙዚቃ በነገሠበት የአምስት አስርት ዓመታት ቆይታውም አይረሴ የሚባሉ ሙዚቃዎችን ለአድማጭ አበርክቷል።

‘እወድሻለሁ’፣ ‘ትዝ ባለኝ ጊዜ’፣ ‘የከረመ ፍቅር’፣ ‘ውበትም ይረግፋል’፣‘አትጥፊ ከጎኔ’ እና ሌሎችን ዘመን ተሻጋሪ ሙዚቃዎችን የተጫወተው ጌታቸው ምን ያህል ዘፈኖችን እንደሠራም በትክክል ቁጥሩን እንደማያውቀው በአንድ ወቅት ተናግሮ ነበር።

ጌታቸው ለየት ባለ ድምጹ እና ቅላጼው፣ በመድረክ ውዝዋዜው፣ የአዘፋፈን ስልቱ የራሱን ዐሻራ በኢትዮጵያ የሙዚቃ መድረክ መፍጠር የቻለ አርቲስት እንደሆነ ይነገርለታል። ወርቃማ ተብሎ በሚጠራውም የኢትዮጵያ የሙዚቃና የሥነ ጥበብ ታሪክ ላይ አስተዋጽኦ ማድረጉንም ይመሰክሩለታል።

ሙዚቀኛው ለ28 ዓመታት ገደማ ኑሮውን በአሜሪካ አድርጎ የነበረ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያም የተመለሰው ከአስር ዓመት በፊት ነበር። ወደ ኢትዮጵያም ከተመለሰ በኋላ በተለያዩ መድረኮች ሥራውን ያቀርብ ነበር።

በአዲስ አበባ መርካቶ አካባቢ ተወልዶ ያደገው ጌታቸው ሙዚቃን መጫወት የጀመረው ገና በልጅነቱ ነበር። አንጋፋው ሙዚቀኛ ጌታቸው የአንዲት ሴት ልጅ አባት ነበር።

# ስተገልጋይ ክብር የነፈገው ተቋም

በጋዜጣው ሪፖርተር

ፓስፖርት ፈልገው ወይም በሥራ ምክንያት ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ጎራ ካሉ ረዥም ሰልፍ እና መጨናነቅ ማየት የተለመደ ነው። የሰልፍ አሰላፊዎች ዱላም ሊያጋጥም ይችላል።

ወጣት፣ ሴት፣ ወንድ፣ ልጅ ያዘሉ እናቶች እንዲሁም «ፓስፖርት ፈልገው ነው?» እያሉ እግር በእግር የሚከተሉ ሕገወጥ ደላሎችም በአካባቢው ውር ውር ይላሉ። የፓስፖርት አሰጣጥ ሂደቱን ለመመልከት በመሥሪያ ቤቱ የተገኙት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዘጋቢዎችም ይህንን መመልከት ችለዋል፣ ሆኖም በወቅቱ መረጃ ለመሰብሰብ ያደረጉት ሙከራ በፖሊሶች ክልከላ ምክንያት አልተሳካም።

አገልግሎቱ 24 ሰዓት የፓስፖርት ህትመትና በበይነ መረብ ምዝገባ አሠራር ዘርግቻለሁ ቢልም አሁንም በርካታ ተገልጋዮችን አገልግሎቱ ደጃፍ ላይ መመልከት አልቀረም።

ተገልጋዮች ዐሻራ ለመስጠት እና ፎቶ ለመነሳት በመሥሪያ ቤቱ መገኘት ግዴታቸው በመሆኑ ከተለያዩ አካባቢዎች መጥተው በወረፋው ምክንያት ላልተፈለገ እንግልት ይዳረጋሉ። እንግልቱ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ከጥሩ እንቅልፍ ተነስቶ ረዥም ሰልፍ ከመሰለፍ ይጀምራል። በሌቦች መዘረፍም የሚያጋጥም ክስተት መሆኑን ተገልጋዮች በምሬት ይናገራሉ።

ለአላስፈላጊ እንግልት እና ወጪ ተዳርገናል የሚሉ ተገልጋዮች ሃሳባቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሲገልጹ አዲስ ፓስፖርት ለማውጣት በበይነ መረብ አማካኝነት ከተመዘገቡ ወራት እንዳለፋቸው ይገልጻሉ።

ተገልጋዮቹ አገልግሎቱ አካባቢ ወረፋ ለመያዝ ስንሞክር «እኔ ቅድሚያ ወረፋ ልያዝላችሁ ክፈሉኝ» በሚሉ ደላሎች እንዋከባለን ይላሉ። እነሱ እንደሚሉት የመሥሪያ ቤቱን ሰልፍ አሰላፊዎች ወከባና ዱላ አልፎ ውስጥ መግባት መቻል መታደል ነው።

ተገልጋዮቹ በሌሊት ለመነሳት ሲሉ በአካባቢው ለአልጋ ኪራይ ከፍለው እንደሚያድሩና ለአላስፈላጊ ወጪም እንደሚዳረጉም ይገልጻሉ። ሰልፉ ረዝሞ ወረፋ ሳይደርሳቸው ከቀረም ቅጣት እንደማይቀርላቸው ይናገራሉ።

የፓስፖርት አሰጣጥ ሂደቱ ተስተካክሏል ይባል እንጂ አሁንም ችግሮቹ እንደነበሩ ናቸው የሚሉት ፎቶ ለመነሳት በተሰጣቸው ቀጠሮ በአገልግሎቱ እንደተገኙ የሚናገሩት አቶ ቀለሙ ተረፈ (ስማቸው የተቀየረ) ናቸው።

አሠራሩ ዘመናዊ ሆኗል የሚባል መረጃ በመስማታቸው የተቀላጠፈ መስተንግዶ ጠብቀው ወደ አገልግሎቱ እንደሄዱ የሚናገሩት ተገልጋዩ፤ በአገልግሎቱ የተመለከቱት ግን በአካባቢው ያለውን በርካታ አገልግሎት ፈላጊ ሕዝብ በተገቢው መንገድ ከማስተናገድ ይልቅ በዱላ በመደብደብ ሥርዓት ለማስያዝ ሲሞከር መሆኑን ይገልጻሉ።

ወደ መግቢያ በሩ ተጠግቶ መረጃ ማግኘት የማይታሰብ እንደሆነም ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት በዱላ ከምደበደብ አገልግሎቱ ይቅርብኝ ብለው ተመልሰዋል። የፓስፖርት አሰጣጥ ሂደቱ ሳይዘምን እንደዘመነ አድርጎ ማስተዋወቅም ፍጹም ተገቢነት እንደሌለውና ሕዝብ በለውጥ እንዳያምን እንደሚያደርግም ይናገራሉ።

ሌላኛው ተገልጋይ አቶ ጌታቸው መኩሪያ (ስማቸው የተቀየረ) በአገልግሎቱ መግቢያ በር ላይ ያለውን ረጅም ሰልፍ እና እንግልት በትዕግስት አልፈው ወደ ውስጥ ቢገቡም መልካም መስተንግዶ እንዳላጋጠማቸው ይናገራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት የአገልግሎቱ ሠራተኞች ቁጣ ትዕግስትን የሚፈታተን ነው።

ከጉዳያቸው ጋር ግንኙነት የሌለው ጥያቄ መጠየቃቸውን እና እናትና አባታቸው በሕይወት እንደሌሉ በመናገራቸው ከአባታቸው ወይም ከእናታቸው የትውልድ ስፍራ የቅርብ ዘመድ መታወቂያ ኮፒ ካላመጡ እንደማይስተናገዱ እንደተነገራቸው ይገልጻሉ። መታወቂያ ኮፒ የማመጣበት ምንም የስጋ ዘመድ ስለሌለኝ ከከፈልኩ በኋላ ፓስፖርት እንዳላገኝ ተደርጌያለሁ ይላሉ አቶ ጌታቸው። በአገልግሎቱ ቅሬታ የሚቀርብበት አሠራርም በግልጽ እንደሌለ በምሬት ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም አጠቃላይ የቀረቡትን ቅሬታዎች መነሻ በማድረግ የተቋሙን የሥራ ኃላፊ ለማነጋገርና ለተገልጋዮች በቂ መረጃ ለመስጠት በስልክ፤ በአካልና በደብዳቤ ጭምር ጥያቄ አቅርቦ ነበር። ሆኖም የተቋሙ ኃላፊ ስለጉዳዩ ምላሽ ለመስጠት አልፈቀዱም። በመጨረሻ ግን የተቋሙ የኮሙኒኬሽን ዳሬክተር ወይዘሮ ማስተዋል ገዳ ምላሽ ሰጥተውናል።

ወይዘሮ ማስተዋል ተገልጋዮች ወደ ተቋሙ በሚመጡበት ወቅት በክብር መስተናገድ እንዳለባቸው ያምናሉ። ተገልጋዮችን በአግባቡ ባለማስተናገድ የዲሲፕሊን ችግር ያለባቸው ሠራተኞች ላይ እርምጃ እየተወሰደ እንደሆነም ይገልጻሉ። በቀጣይም እንዲህ ዓይነት ችግሮች ሲያጋጥሙ እርምጃ ይወሰድ ዘንድ ተገልጋዮች ቅሬታ ሲኖራቸው ቅሬታ ለተቋሙ ማቅረብ አለባቸው ይላሉ። ለተቋሙ ሠራተኞች ደንበኞችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ሥልጠናም እንሰጣለን ይላሉ ወይዘሮ ማስተዋል።

ዳይሬክተሯ ተገልጋዮች አዲስ ፓስፖርት ፈልገው በድረ ገጽ ሲያመለክቱ ፎቶግራፍ የሚነሱበትን እና ዐሻራ የሚሰጡበትን ቀንና ሰዓት የሚያሳውቅ በመሆኑ ተገልጋዮች በሰዓቱ ብቻ ቢመጡ ሰልፉ ሊቀንስ እንደሚችል እንዲሁም የተቀጠሩ ተገልጋዮች ሳይስተናገዱ እንደማይቀሩም ይናገራሉ።

በአካባቢው መጨናነቅ የሚፈጠረው ቀጠሮ ባላቸው ተገልጋዮች ብቻ ሳይሆን «ፓስፖርት ዘግይቶብናል» ብለው ለመጠየቅ በሚመጡ ተገልጋዮች እና አንድ ጉዳይ ለመጨረስ ከአንድ በላይ ሰው ስለሚመጣ እንደሆነም ይገልጻሉ።

ተገልጋዮች ከሌሊቱ 10 ሰዓት ተሰልፈው ለዘራፊዎች እንዳይጋለጡ ሰልፉ በሥራ ሰዓት ብቻ እንዲሆን በአገልግሎቱ በኩል የታሰበ ነገር ካለ የተጠየቁት ዳይሬክተሯ የሌሊት ሰልፉ ከአገልግሎቱ እውቅና ውጪ መሆኑንና ለሰልፉ ሰዓት የመገደቡን ጉዳይ በቀጣይ በጋራ የሚታይ ነገር እንደሚሆን ነው ምላሻቸውን የሚሰጡት።

በመሀል ጉዳይ አስፈጻሚ ደላሎች አሉ ስለሚባለው የተጠየቁት ዳይሬክተሯ አንዳንዴ በውጭ እና በማኅበራዊ ሚዲያ ያሉ ደላሎች አስቸኳይ ፓስፖርት እናሰጣለን በሚል ኅብረተሰቡ ለተለያየ ወጪ እየተዳረገ እንደሆነ ጥቆማዎች ለተቋሙ ይደርሳሉ ይላሉ። ይህንንም የተቋሙ የጸረ ሙስና ዳይሬክቶሬት የሚያጣራበት ሥርዓት እንዳለውም ይናገራሉ።

ተገልጋዮች ለአስቸኳይ ፓስፖርት በሕገ ወጥ ደላሎች በኩል ለማስጨረስ ከመሞከር ይልቅ እራሳቸው በጥቂት ቀናት መጨረስ እንደሚችሉ ነው ዳይሬክተሯ የሚናገሩት።

ተገልጋዮች እንግልቱን ለመቀነስ ለአስቸኳይ ፓስፖርት ካልሆነ በስተቀር አቅራቢያቸው ባለው የአገልግሎቱ ጽሕፈት ቤት በኩል ቢያመለክቱ ሰልፍና መጨናነቁ ይቀንሳል ሲሉ ምክራቸውን ይለግሳሉ።

እሳቸው ይህንን ቢሉም በተቋሙ በር ላይ ያለው ሰልፍም ሆነ የተገልጋዩ ምሬት ግን አሁንም እንደቀጠለ ነው። ዘላቂ መፍትሔም ይሻል።

# የኢትዮጵያ እና ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በቅርቡ በተካሄደው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ የተሳተፉት የሶማሊላንድ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ እና ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር ዶክተር ኢሳ ካይድ መሐሙድ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ሶማሊላንድ ከዐረብ ሊግና ከግብጽ የሚወጡ መግለጫዎች አያሳስባትም። ምክንያቱም በሶማሊላንድና በኢትዮጵያ መካከል የሚደረጉ ስምምነቶች በሦስተኛ አካላት ሊቀየሩ ወይም ሊለወጡ አይችሉም።

ሶማሊላንድ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የባህር ስምምነት በተመለከተ የውጭ ጣልቃ ገብነቶችን እንደምትቃወም እንዲሁም ሂደቱ በውጭ አካላት እንደማይቀየር የገለጹት ዶክተር ኢሳ፤ ሶማሊላንድና ኢትዮጵያ የተፈራረሙት የባሕር በር የመግባቢያ ስምምነት ነው ብለዋል።

ሥምምነቱን ዳር የሚያደርስ ቴክኒካል ኮሚቴ ማዋቀር፣ ዓለም አቀፍ የሕግ ባለሙያዎች ቡድን ማደራጀት እና ከፍተኛ የሕገ መንግሥት አማካሪ ግብረ ኃይል የማደራጀት ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቁመዋል፡፡

ቡድኑ የስምምነቱ ሂደትና ሕግ ላይ የተለያዩ ጥናቶችን እያከናወነ ነው። ይህም በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ እና ለሁለቱም ሀገራት አብሮ የማደግ ዕድል ይዞ የሚመጣ ይሆናል።

በሁለቱ ሀገራት መካከል የጋራ ድንበር በመኖሩ የሕዝብ ለሕዝብ ውህደት መኖሩን የገለጹት ዶክተር ኢሳ፤ ይህም ግንኙነት ከመግባቢያ ሰነዱ በኋላ አልተጀመረም። ይልቁንም ረጅም ጊዜ የቆየና የሚቀጥል ነው። ስምምነቱ የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ ነው። ይህም የሁለቱን ሀገራት ንግድና አጠቃላይ ኢኮኖሚ ያሳድጋል ብለዋል።

የኢትዮ-ሶማሊላንድ የመግባቢያ ስምምነት ከዓለም አቀፍ ሕግና ከሁለትዮሽ የንግድ እንቅስቃሴ ጋር የሚስማማ ነው ያሉት ዶክተር ኢሳ፤ ከኢትዮጵያ ጋር የተደረገው የመግባቢያ ስምምነት ፍጹም ሕጋዊ እና ሕጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

የበርበራ ወደብን ፋሲሊቲዎች ማስፋፊያና ማዘመን እንዲሁም የበርበራ ኮሪደርን የማገናኘት ሥራ የጀመርነው በዚሁ መነሻ ነው ያሉት ዶክተር ኢሳ፤ ይህ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚፈጀውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ከተባበሩት ዐረብ ኤምሬቶች ዱባይ ፖርትስ ወርልድ ጋር በትብብር እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል።

# «ሰላምና ልማትን አምጥቶ በፍቅር ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለዚህ ደግሞ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች እንዲሁም ወጣቶች መሥራት ይኖርባቸዋል ነው ያሉት።

በመንግሥት አቅም የሚመለስ ካለ ተመልሶ፤ የማይመለስ ነገር ካለ ደግሞ ሕዝቡ በሚሰማው መንገድ ጊዜ ሰጥተን እንፈተዋለን ብለዋል።

«በውስጣችን ያለውን ችግር ብንፈታው ጥሩ ነው» በማለት፤ በየሰፈሩ ያለውን ለውይይት በማቅረብ ይቅርታ በመባባል፤ ካሳም ካስፈለገ ካሳ ተከፍሎ መታረቅና መስማማት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ለተነሱ ችግሮች ሁሉ ምላሽ መስጠት የሚቻለው መንግሥት ፋታ አግኝቶ ሥራ መሥራት ሲችል እንደሆነም ገልጸዋል።

በንጹህ ልብ ሀገራችንን ወድደን ማገልገል እንፈልጋለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ያማረች ኢትዮጵያን ብቻ ነው ማየት የምንፈልገው ሲሉ ጠቅሰዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ገለፃ፤ መንግሥትን ማገዝ ይገባል። የሸፈቱና የወጡትን ተባብሮ መመለስም ይኖርብናል።

የመንግሥት ፍላጎት በአማራ ክልልም ሆነ በኦሮሚያ ክልል ያለው የጦር መሣሪያ ትግል፣ ማገትና መግደል ወደ ሰላማዊ መንገድ እንዲመጣ መሆኑን አመላክተዋል።

ከዚህ ቀደም በክልሉ ጉዳይ ከተለያዩ አካላት ጋር ውይይት ማድረጋቸውንና በውይይቱ ከሚነሱ ጉዳዮች አንዱ ሕገ መንግሥቱ ይሻሻል የሚል ጥያቄ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ሰዎች በመጡና በሄዱ ቁጥር ሀገር ታሪኳ እየፈረሰና ሕገ መንግሥት እየተቀያየር መሄድ የለበትም በሚል ዕሳቤ አብዛኛውን መልስ በሚመልስ መልኩ ለመሥራት፤ ሌሎችም መሰል ጥያቄ እንዳያነሱ ሚዛናዊነቱን ለማስጠበቅ ተቋም ቢቋቋምም፤ ይህን ላለመቀበል እንቅፋቶች እንዳጋጠሙ ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወሰን ጥያቄን በሚመለከት በሰጡት ምላሽ፤ በአማራና በትግራይ ክልል ሁልጊዜ ጭቅጭቅ የሚነሳባቸው ቀበሌዎችና ወረዳዎች ነበሩ። አሁን ውጊያ ከተፈጠረ በኋላ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ አመራር ተሰብስቦ የወልቃይት ጉዳይ የሚያባላ ጉዳይ እንዳይሆን በሕግ እንዲቋጭ፤ ተፈናቃይን ቦታው ላይ በመመለስና ራሳቸው የወልቃይት ሰዎች በቀበሌና በወረዳ ምርጫ አካሂደው ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድሩ፤ መከላከያ ሰላም ያስከብር፤ ሲረጋጋና ጊዜው ሲፈቅድ የሁለቱም ክልሎችና ዓለም አቀፍ ታዛቢ ባለበት ሕዝቡ ሕዝበ ውሳኔ ያድርግ ተብሎ ውይይት ተደርጎ እንደነበር አንስተዋል።

ኮሚቴ ተዋቅሮ ወልቃይትና ራያ መላኩንም አስታውሰዋል። በዚህም ሕዝቡ ራሱ መወሰን እንዳለበት ምላሽ ተገኝቶ እንደነበር ጠቅሰዋል። አሁንም የሚሻለው በስምምነትና በሕዝብ ውሳኔ ተስማምቶ መኖሩ ነው ሲሉም ተናግረዋል። በውይይት ከሆነ መፍትሔ እንደሚያገኝ አስታውቀዋል።

«ያሉትን ችግሮች አንድ መሆናችንና ኢትዮጵያዊ መሆናችንን በማያሳጣ መንገድ ማየት ያስፈልጋል። የምንወደውን ሰላምና ልማት እንኑረው። ይህን ማድረግ ከቻልን ችግሮችን እናልፋለን» ነው ያሉት።

ከመልካም አስተዳደር ችግርና ሌብነትን ከመከላከል አንጻር ባነሱት ሃሳብ፤ ፓርቲ የጠራ ከሆነ፤ የጠራ አመለካከት ካለውና ሃሳቡ አንድ ከሆነ ብዙ ጉዳይ መፈታት እንደሚችል ተናግረዋል። ሁሌ ውይይት የሚደረገውም ለዚሁ እንደሆነ አመላክተዋል።

ሌብነትን የመታገል ሥራ ከተጀመረ ወዲህ ነገሮች አስቸጋሪ እየሆኑ መምጣታቸውን ጠቅሰው፤ ይህን ለመታገል ብዙ ቢሠራም አሁንም ግን አላለቀም። ለዚህ ሁሉም ማገዝ ይኖርበታል ብለዋል።

ከዚህ ባሻገር ተፈናቃዮችን በሚመለከት፤ ዜጎች ከሞቀ ጎጇቸው ወጥተው በካምፕ ውስጥ መቀመጥ እንደሌለባቸውና ይህንን ችግር ለመፍታት ዜጎች ወደ ቀደመ መኖሪያ ስፍራቸው እንዲመለሱ ጥሪ ቢቀርብም ለፖለቲካ መጠቀሚያ በሚያደርጓቸው አካላት እንዳይመለሱ እንቅፋት መፈጠሩን ጠቅሰዋል። አሁንም ቢሆን ከየትኛውም አካባቢ የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቀዬአቸው ተመልሰው መኖር እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

ሃይማኖትን በሚመለከት፤ «በመንግሥት ፖሊሲና እውቅና የትኛውንም ሃይማኖት ለመጉዳት አስበን አናውቅም» ብለዋል። ተቋማቱም ቢሆኑ ሃይማኖተኛንና ፖለቲከኛውን መለየት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል።

በመሠረተ ልማት፤ በማዳበሪያ አቅርቦትና መሰል ችግሮች መንግሥት ብዙ ሥራዎችን በክልሉ እየሠራ እንዳለና ይህ በቂ ባለመሆኑም በቀጣይ በርካታ ችግሮችን ለመፍታት በትኩረት እንደሚሠራ አንስተዋል።

በተለይ ከሲሚንቶ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ለመቅረፍ ኢትዮጵያ የምታመርተውን ሲሚንቶ 50 በመቶ የሚሸፍን ፋብሪካ በሰሜን ሸዋ ዞን መሠራቱንና ይህም በቅርቡ እንደሚመረቅ ገልጸዋል።

# ኢትዮጵያና ኬንያ በሰባት አዳዲስ የትብብር መስኮች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሰባት የተለያዩ አዳዲስ የትብብር መስኮች በጋራ ለመሥራት የሚያስችሉ የመግባቢያ ስምምነቶችን ተፈራርመዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ታዬ ገለጻ፤ በስብሰባው የቆየውንና ጠንካራ የነበረውን የሁለቱን ሀገራት ዲፕሎማሲዊ ግንኙነት በሁሉም ደረጃ ለማስቀጠል ከስምምነት ተደርሷል። በውጭ ጉዳይና መከላከያ ዘርፎች፣ በንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፎችና በማኅበራት ዘርፎች ሰባት አዳዲስ ስምምነቶችን ተፈራርመናል።

ስምምነቶች በፖለቲካና ደህንነት፣ በባህል፣ በዱር እንስሳት ጥበቃ፣ በቱሪዝም፣ በ«ብሉ ኢኮኖሚ»፣ በግብርናና ዓሣ ሀብት፣ በፐብሊክ ሰርቪስና አቅም ግንባታ መስኮች መሆኑን ገልጸዋል። እንዲሁም ቀደም ሲል በተስማሙባቸው ስምምነቶች አፈጻጸም ዙሪያ ውይይት መደረጉን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያና ኬንያ ልዩና ሁሉን አቀፍ ትብብር ለማጠናከር እየሠሩ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ በሁለቱ ሀገራት ግንኙነት መካከል፣ በቀጣናዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ይሠራሉ። የኢትዮጵያና ኬንያ ሕዝቦች በባህል፣ ቋንቋ፣ በታሪክ የተሳሰሩና ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ግንኙነት እንዳላቸውም አስታውቀዋል።

የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ 36ኛ ዙር ደርሷል ያሉት ሚኒስትሩ፣ ይህም የሁለቱን ሀገራት ልዩ ትብብርና ጠንካራ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ያመለክታል ሲሉ ገልጸዋል።

አየር ንብረት ለውጥ፣ ሽብርተኝነት፣ ሥራ አጥነት፣ ሕገወጥ ስደትና መሰል ችግሮች የጋራ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በጋራ መሥራት እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል። ኢትዮጵያ ከኬንያ ጋር ያላትን ትብብር በሰላምና በልማት ማጠናከር እንደምትፈልግም አምባሳደር ታዬ ገልጸዋል።

የኬንያ የውጭ ጉዳይ እና የዲያስፖራ ጉዳዮች የካቢኔ ፀሐፊ ዶክተር ሙሳሊያ ሙዳቫዲ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ 36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ውጤታማ ሆኖ በመጠናቀቁ ምስጋና አቅርበዋል። እንዲሁም ኢትዮጵያ 37ኛው የአፍሪካ ኅብረት ጉባዔ በስኬት ማስተናገዷን በመግለጽ፤ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ስምምነቱ የሁለቱን ሀገራት የሁለትዮሽ ትብብር ይጠናከራል ያሉት የካቢኔ ፀሐፊው፤ ሁለቱ ሀገራት ግንኙነቶችን ማስፋት በሚችሉባቸው በውጭ ጉዳይና መከላከያ ዘርፎች፣ በንግድና ኢንቨስትመንትና በማኅበራት ዘርፎች ተጨማሪ ስምምነቶችን ተፈራርመዋል። ሽብርተኝነትን በመከላከልና የቀጣናውን ሰላም በማስፈን ረገድ ሁለቱ ሀገራት በጋራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ሙሳሊያ ገለጻ፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል የሚደረጉ የንግድ ልውውጥ ከሁለቱ ሀገር ባለፈ ቀጣናዊ ትስስርን ያጠናክራል። ቀጣናዊ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ኢትዮጵያና ኬንያ በጋራ ይሠራሉ። አዲስ የተፈረሙት የመግባቢያ ሰነዶች ለሁለቱ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት ትልቅ ሚና አላቸው።

ስምምነቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ይገባል ያሉት ዶክተር ሙሳሊያ፤ በጋራ የድንበር ቁጥጥር ዙሪያ፣ በግጭት አፈታት፣ በስደተኞች፣ ድንበር ተሻጋሪ ሽብርተኝነትን በመከላከል ረገድ የጋራ ሥራዎችን ለመሥራት ኬንያ አስፈላጊውን እገዛ ታደርጋለች። እንዲሁም በሁለትዮሽ፣ በቀጣናዊና በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ከኢትዮጵያ ጋር ለመሥራት ኬንያ ዝግጁ መሆኑኗ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ውይይቱ የአማራ ክልል ሰላምን ለማጽናት ተጨማሪ አቅም ይሆናል!

የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም በማረጋገጥ የመላው ሕዝባችን መሻት የሆነውን ልማት ለማስፈን ሰፊ ሥራዎችን ሠርቷል። ጠብመንጃ አንስተው የትጥቅ ትግል ውስጥ የነበሩ ኃይሎችን ጨምሮ በፖለቲካ እሳቤያቸው ምክንያት ለስደት የተዳረጉ ዜጎች ወደሀገራቸው ገብተው የፖለቲካ ትግላቸውን በሰላማዊ መንገድ ተግባራዊ የሚያደርጉበትን አዲስ የፖለቲካ ባህል ፈጥሯል።

ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰላም የመኖር መርህ በተለይም ከኤርትራ ጋር የነበረውን ውጥረት በዚሁ መንፈስ በመቃኘት ለሁለት አስርት ዓመታት ያለ መፍትሔ የቆየውን የኢትዮ- ኤርትራ ችግር በሰላማዊ መንገድ ፤ በወንድማማችነት መንፈስ በመፍታት በቀጣናው የነበረውን የግጭት ስጋት ማስወገድ ችሏል። በዚህም ሰላም ከሀገር ባለፈ ለቀጣናው ሕዝቦች ሰላም ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ በተጨባጭ ማሳየት ችሏል።

ይህም ሆኖ ግን መንግሥት ረጅም ርቀት የሄደበት የሰላም መንገድ ብዙም ሊራመድ አልቻለም። መንግሥት ይዞት የመጣውን አዲስ የፖለቲካ እሳቤና መንገድ ከመጣንበት ኋላቀር የፖለቲካ ባህል / ከአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት በመመዘን የአቅመቢስነት መገለጫ አድርገው የወሰዱ ኃይሎች እንደ ሀገር የተፈጠረውን ይህን መልካም አጋጣሚ በአግባቡ ሳንጠቀምበት ተመልሰን ወደ ግጭት አዙሪት እንድንገባ አድርገውናል።

በዚህም እንደሀገር የፈለግነውን ልማት ከማስፋት ይልቅ ወዳልተገባ ጦርነት ገብተን በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለሞትና ለአካል ጉዳት፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለስደትና ለመፈናቀል፤ በቢሊዮን የሚቆጠር ሀብትም ለውድመት ተዳርጓል። ይህም እስከ አሁን ባልተሻገርነው ሀገራዊ ስብራት ውስጥ ለመቆየት የተገደድንበት ታሪካዊ ክስተትን ፈጥሯል።

ይህንን ክስተት በመጠቀምም የለውጡ መንፈስና ጉዞ ያልተመቻቸው የውጭና የውስጥ ኃይሎች በመቀናጀት፤ ሀገርን እንደ ሀገር የህልውና ስጋት ውስጥ የከተቱበት ሁኔታ ተፈጥሯል ። ይህንን ስጋት ለመቀልበስ በተደረገው ጥረትም መላው ሕዝባችን ባለው አቅም ሁሉ ክቡር መስዋዕትነት ከፍሏል። በዚህም ሀገርን መታደግ ብቻ ሳይሆን ከአፍራሽ አደጋ መከላከል የሚያስችል አቅም መገንባት ተችሏል።

የሰላም ሐዋርያ ከመሆን ባለፈ፤ ዘላቂ ሰላምን በማስፈን ልማትን አስተማማኝ ለማድረግ የሀገሪቱን የመከላከያ እና የጸጥታ ኃይሎችን አቅም በመገንባት፤ በሁለንተናዊ መንገድ ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት የሚችሉበትን ቁመና እንዲላበሱ በስፋት በመሥራት ሀገሪቱን ከህልውና ስጋት አውጥቶ አስተማማኝ በሆነ የህልውና መሠረት ላይ ማቆም ችሏል።

በዚህ ሂደት ውስጥም ለሰላም ካለው ከፍ ያለ መሻት አንጻር፤ በግጭት ወቅቶች ሳይቀር ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት፤ የተደጋገሙ የሰላም ጥሪዎችን በማቅረብ በተጨባጭ አሳይቷል። ከአሸናፊ ተሸናፊ ትርክት ወጥቶ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ለዘለቄታው እንዲቋጩ ካለው የጸና እምነት የተነሳም ተነሳሽነቱን ቀድሞ በመውሰድ የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት እውን እንዲሆን ረጅም መንገድ ተጉዟል።

ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላም የሚያጋጥሙ፤ ስምምነቱን የሚጎዱ ተግባራትን በሆደ ሰፊነት በማለፍ፤ ለስምምነቱ ተፈጻሚነት ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ መላው ሕዝባችን ከጦርነት ሊያተርፈው የሚችለው አንዳች ነገር እንደማይኖር በተግባር አሳይቷል፤ እያሳየም ነው።

በተመሳሳይ መልኩ በተሳሳተ እሳቤና ባልተገባ ትርክት በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል ከሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ጋር በውይይት ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚያስችሉ የሰላም ጥሪዎችን በማቅረብ፤ ለሰላማዊ ድርድር ዝግጁ መሆኑን በተለያዩ ወቅቶች አስታውቋል።

ለሰላም ካለው የጸና አቋም በመነሳት ከአሸባሪው ሸኔ ጋር በሰላማዊ መንገድ በውይይት ችግሮችን ለመፍታት ከአንድም ሁለት ጊዜ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች በተገኙበት ድርድሮችን አድርጓል። በየወቅቱም በተለያዩ መንገዶች ለቡድኑ የሰላም ጥሪዎችን በማድረግ፤ በአካባቢው ሰላም ሰፍኖ ሕዝቦች የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያለውን ቁርጠኝነት አሳውቋል።

ይህ የመንግሥት ሰላም ቁርጠኝነት አሁንም የተጠበቀ ስለመሆኑም በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው፤ ከአባላቱ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ በሰጡበት ወቅት በግልጽ አስታውቀዋል። ይህ የመንግሥት አቋም መቼም እንደማይለወጥ አመላክተዋል።

መንግሥት ገና ከጅምሩ በአማራ ክልል የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ኃይሎች ለሕዝቡ የሰላምና ልማት ፍላጎት ተገዥ በመሆን፤ ከጥፋት መንገዳቸው ወጥተው አሉ የሚሏቸውን ችግሮች በሰላማዊ መንገድ በውይይት መፍታት የሚቻልበት የሰላም መንገድ መኖሩን በተደጋጋሚ አስታውቋል። በጉዳዩ ዙሪያ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶችን ሳይቀር በማሳተፍ በክልሉ ያለው ችግር በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ በቁርጠኝነት ተንቀሳቅሷል።

ሕዝቡ ለሰላምና ለልማት ካለው ፍላጎት የተነሳ በክልሉ በየጊዜው መሻሻሎች ቢኖሩም የአማራ ሕዝብ ከሚፈልገው ልማት አንጻር የሰላም ጉዳይ አሁንም የክልሉ ዋነኛ አጀንዳ ነው። ከዚህ አንጻር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሰሞኑን ከአማራ ክልል ሁሉም ዞን ከተውጣጡ ተወካዮች ጋር ያደረጉት ውይይትና ከውይይቱ በኋላ የተደረሰበት ስምምነት በክልሉ የተሻለ ሰላም ለማስፈን ተጨማሪ አቅም እንደሚሆን ይታመናል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የካቲት 12 ሲታወስ

**በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

መቼም ስለ የካቲት 12፣ 1929 የፋሺስት የአዲስ አበባ ጭፍጨፋ በተወሳ ቁጥር በግንባር ቀደምነት ከሚጠቀሱ መጽሐፍት የኢያን ካምቤል ፤"THE MASSACER OF ADDIS ABABA"ይገኝበታል። የወቅቱ የጣሊያን ፋሽስት መሪ ቢኒቶ ሙሶሊኒ ፋሽዝምን በመላው ዓለም ለማስፋፋት ካለው የቀን ቅዠትና በሀገሬው ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና ድጋፍ ለማሳደግ ሲል ኢትዮጵያን ወረረ።

ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በኋላ ቀር የጦር መሣሪያ፣ በጦር ፣ በጎራዴና በጋሻ ለተከታታይ ስምንት ወራት ገትረው ቢዋጉም፤ የፋሽስቱን የመርዝ ጭስ፣ የአውሮፕላን ድብደባና ሜካናይዝድ ጦር መቋቋም ባለመቻላቸው አዲስ አበባን በፋሽስት እጅ ከመውደቅ አላዳኗትም ። ወረራው በሌላ በኩል የመንግሥታቱን ማኅበር/League of Nations/ከማኮስመኑ ባሻገር የ2ኛውን የዓለም ጦርነት ወደ አዲስ ምዕራፍ አሸጋገረው ይለናል ኢያን በዚህ ገራሚ መጽሐፉ።

ሰላማዊ ዜጎች በፋሽስቱ ጎልቶ መሳፍርት የሌለው ሰቆቃና ጭፍጨፋ አለቁ። የሚያሳዝነው አዲስ አበባ እንዲህ በደም ጎርፍ ስትታጠብ አብዛኛው ዓለም መረጃው አልነበረውም። የሚያውቁም ስለጉዳዩ እንዲነሳ ካለመፈለጋቸው ባሻገር የወራሪውን ፋሽስት ግፍ ደፍሮ ያወገዘ አልነበረም። የፋሽስት ወታደሮች ጭፍጨፋውን የፈጸሙት በተቻላቸው መጠን ምንም ዓይነት መረጃ እንዳይወጣ ብርቱ ጥንቃቄ በማድረግ ነው።

በአዲስ አበባና በአካባቢው የሰዓት እላፊ በመጣል፤ የስልክ አገልግሎትን በማቋረጥ፤ ማንም ከአዲስ አበባ እንዳይወጣ በመከልከልና ከእነሱ ውጪ ካሜራ ይዞ የተገኘን የውጭ ሀገር ዜጋን ሳይቀር በመቀማት፤ ጭፍጨፋው ሲፈጸም ያዩ ኢትዮጵያውያን ሳይቀር ሆን ተብሎ ተገድለዋል። ጭፍጨፋውን በፊትአውራሪነት የመሩና ያስተባበሩ አብዛኞዎቹ የፋሽስቱ አዛዦችም ሆን ብለው መረጃ በጽሑፍም በፎቶም አላስቀሩም። ሌላው ይቅርና ወደ ሮም የላኩት መረጃ የለም። ቢኖርም እምጥ ይግባ ስምጥ አይታወቅም ይለናል ኢያን መጽሐፉን ለማዘጋጀት የገጠመውን ፈተና ሲገልጽ።

> **ጀግኖች አርበኞች በዱር ገደሉ ተዋድቀው የጣሊያን የአምስት አመቱ ቆይታ በሽንፈት ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ እንግሊዝ ጣሊያን በጦር ወንጀለኝነት እንድትጠየቅ ስለማትፈልግ ስለ ጭፍጨፋው በመረጃነት የሚያገለግሉ ማስረጃዎችን ኢትዮጵያ እንዳታገኝ ሰነዶችን ከመደበቅ አንስቶ ክልከላ እያደረገች በሌላ በኩል ደግሞ የፋሺስቱ ተጠርጣሪዎች በመንግሥታቱ ማኅበር የጦር ወንጀል ኮሚሽን እንደሚከሰሱ የማይጨበጥ ተስፋ በመስጠት ንጉሡን የማዘናጋት ሥራ ሠርታለች**

ጀግኖች አርበኞች በዱር ገደሉ ተዋድቀው የጣሊያን የአምስት አመቱ ቆይታ በሽንፈት ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ እንግሊዝ ጣሊያን በጦር ወንጀለኝነት እንድትጠየቅ ስለማትፈልግ ስለ ጭፍጨፋው በመረጃነት የሚያገለግሉ ማስረጃዎችን ኢትዮጵያ እንዳታገኝ ሰነዶችን ከመደበቅ አንስቶ ክልከላ እያደረገች በሌላ በኩል ደግሞ የፋሺስቱ ተጠርጣሪዎች በመንግሥታቱ ማኅበር የጦር ወንጀል ኮሚሽን እንደሚከሰሱ የማይጨበጥ ተስፋ በመስጠት ንጉሡን የማዘናጋት ሥራ ሠርታለች።

ናዚዎች በኑረምበርግ ለፍርድ ቀርበው በአይሁዶች በጂፕሲዎች፣ በሮማዎችና በሌሎች ለፈጸሙት ሰቆቃና ግፍ እንዲሁም በ2ኛው የዓለም ጦርነት በፈጸሙት የጦር ወንጀል ሲጠየቁ ፋሺስቶች ግን ለፈጸሙት የየካቲት 12 የአዲስ አበባና የደብረ ሊባኖስ ጭፍጨፋና ሰቆቃም ሆነ የጦር ወንጀል ተጠያቂ ሳይሆኑ መቅረታቸው የዓለማችንን ፍርደ ገምድልነት ማሳያ ሌላ የታሪክ መታጠፊያ ነው ። በግሌ የአክሱምን ሐውልት ለማስመለስ እንደተደረገው እልህ አስጨራሽ ጥረት ያህል ጭፍጨፋውንና የጦር ወንጀሉን ለዓለም ለማሳወቅ ጥረት ቢደረግ ኑሮ እውቅና ይሰጠውና በጣሊያን መንግሥት ላይም ይቅርታ እንዲጠይቅና ካሳ እንዲከፍል ጫና ማድረግ ይቻል ነበር። ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በግል ጥረት ያደርጉ እንደነበር መረጃ ቢኖረኝም የመጡ የሄዱ መንግሥታት በቂ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ ስላላደረገላቸው ዛሬ ድረስ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም ።

አሁን ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት፤ ከሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር በመቀናጀት የጣሊያን መንግሥት የፋሽስት ወራሪ በሀገራችን ለፈጸመው ግፍና ጭፍጨፋ እውቅና እንዲሰጥና ይቅርታ እንዲጠይቅ ግፊት ሊያደርግ ይገባል። በሀገር ቤትም ትውልድ ይህን አሰቃቂ ጭፍጨፋ እንዲያውቀው ማስተማር ስለሚገባ በሥርዓተ ትምህርቱ ማካተት ያስፈልጋል። ብዙዎቻችንም ስለዚህ ጭፍጨፋ ያለን እውቀትና መረጃ የሚያወላዳ ስላልሆነ መለስ ብለን በወፍ በረር እንቃኝ።

«ራስን ካንገት ላይ፣ ቆራርጦ እየጣለ፤
በችንካር ቸንክሮ፣ ሰው እየገደለ፤
ሰውን ከእነቤቱ ፣ አብሮ እያቃጠለ፤
ማነው እንደ ፋሺስት በሰው ግፍ የዋለ?
ሥጋችንን ገድለው፣ ሊቀብሩት ከጀሉ፤
በዚህ ያልነበሩ፣ ሐሰት እንዳይሉ፤
እሊህ አስከሬኖች ይመሰክራሉ።
ይህን ታላቅ ሥቃይ፣ መከራና ግፍ፤
ሲያስታውስ ይኖራል የታሪክ መጽሐፍ።...»

እነዚህ ስንኞች፡- ከ87 ዓመታት በፊት፣ በፋሺስት ጣሊያን ጭፍራ ማርሻል ሮዶልፎ ግራዚያኒ አማካይነት በአዲስ አበባ ከተማ ከየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. ጀምሮ ለሦስት ቀናት በዘለቀው ጭፍጨፋ ሰማዕት ለሆኑት ከ30 ሺህ ለሚበልጡ ኢትዮጵያውያን በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ዐፀድ በቆመው ሐውልት ግርጌ ከሠፈረው ግጥም የተወሰደ ነው ይለናል «ያቺ የካቲት 12 ቀን ! » በሚል ርዕስ ሔኖክ ያሬድ በአማርኛው ሪፖርተር ከሁለት አመት በፊት ባስነበበን ማለፊያ የሰማዕታት ዝክረ እንጉርጉሮ አዘል መጣጥፉ።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ «የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966» በተሰኘውና በ1989 ዓ.ም በታተመው መጽሐፋቸው እንደገለጹት፣ የጣሊያን ፋሺዝም ጽልመታዊ ገጽታ ቁልጭ ብሎ የወጣው በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ነው። አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የተባሉ ሁለት ወጣቶች በግራዚያኒ ላይ ቦምብ ጥለው ካቆሰሉት በኋላ አዲስ አበባ ላይ መዓት ወረደባት። «ጥቁር ሸሚዝ» እየተባሉ የሚታወቁት የፋሺስት ደቀመዛሙርት መንግሥት አይዟችሁ እያላቸው አዲስ አበባን ቁራ አደረጓት። የሰው ልጅ ጭንቅላት እንደ ዶሮ እየተቀነጠሰ ወደቀ። ቤቶች ከእነ ነዋሪዎቻቸው ጋዩ።

እርጉዝ ሴቶች በሳንጃ ተወጉ። የጭፍጨፋው ተቀዳሚ ዒላማ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በተለይም የጥቁር አንበሳ አባላት ከራስ እምሩ ጋር እጃቸውን ከሰጡ በኋላ በከተማዪቱ ይገኙ ስለነበር በወረንጦ እየተለቀሙ ተረሸኑ።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የካቲት 12…

ከ ገጽ 5 የዞረ

ይህ የምሁራን ጭፍጭፋ አንድ ትውልድ እንዳለ ያጠፋ በመሆኑም በሀገሪቱ የፖለቲካና ምሁራዊ ታሪክ ላይ የማይሽር ቁስል ጥሎ አለፈ።

በዘመኑ የነበሩት ደራሲ ተመስገን ገብሬ «የዓይን እማኙ ሊቀ ጠበብት እውነቱና የካቲት 12» በተሰኘ ጽሑፋቸው እንዲህ ጽፈዋል፡-«ከሦስት ቀን የከተማ ጥፋት በኋላ ከሆለታ የመጡ የፋሺስት አውሬዎች በሚመለሱበት ካሚዮን በኋላው በኩል አቶ አርዓያን እግራቸውን ጠርቅመው አሠሯቸው። ካሚዮኑ ሳይጐትታቸው ‘እኔ ወደ ሰማይ እንድገባ ሰማይ ተከፍቶ ይጠብቀኛል። ኢየሱስንም በዚያ አየዋለሁ። ደስ ይለኛል። ደስ ይለኛል። ደስ ይለኛል!’ የሚለውን የሚሲዮን መዝሙር ዘመሩ። ፋሽስቶቹም የተሻለውን መዝሙር ብትሰማ ይሻልሃል አሏቸውና ዱኪ ዱኪ የሚለውን መዝሙራቸውን ዘመሩ። ካሚዮኑም ሞተሩን አስነስቶ ሲነዳ ታስረው ቁመው ነበርና ያን ጊዜ ዘግናኝ አወዳደቅ አቶ አርዓያ ወደቁ። ካምዮኑም እየፈጠነ ጐተታቸው።

ከአዲስ አበባ እስከ ሆለታ አርባ ኪሎ ሜትር ይሆናል። ካምዮኑ ከዚያ ሲደርስ ያ ከካሚዮኑ ጋር የታሰረው እግራቸው ብቻ እንደተንጠለጠለ ነበርና የካሚዮኑ ነጂ ከካሚዮኑ ፈታና ለውሾች ወረወረው። እኔንም ያለሁበትን ቤት ሰብረው ከዚያ ቤት ያለነውን አውጥተው ከየመንደሩም ሕዝቡን አጠራቅመው አኑረዋል። ከዚያም መህል ጨመሩን። ስምንት መትረየስ በዙሪያችን ጠምደዋል። በዚያም ቦታ ቁጥራቸው በብዙ የሆኑ ሐበሾችን አስቀድመው ገድለዋቸዋል። ሬሳቸውም ተቆላልፎ በፊታችን ነበረ። እኛንም በዚያ ሊገድሉን ተዘጋጁ።

ለመትረየስም ተኩስ እንድንመች ያንዳችንን እጅ ካንዱ ጋር እያይዘው አሰሩን። አሥረውን ወደ መተኰሱ ሳይመለሱ አንድ ታላቅ ሹም መጣ። የርሱም ፖለቲካ ልዩ ነበረ። ፋሺስቶች የሚያደርጉትን የሰላማዊ ሕዝብ መግደል፤ ሕፃናቶችን ከአባትና እናታቸው ጋራ በቤት ዘግቶ ማቃጠል መልካም ብሎ ቢወድ እንኳን እኒያ ቦምብ በቤተ መንግሥቱ ስብሰባ የወረወሩት ሐበሾች ሳይታወቁ እንዲቀሩ አይወድም ነበርና ስለዚህ ካሚዮኖች ይዞ እየዞረ ፋሽስቶች የሚገድሉትን እያስጣለ ወደ እስር ቤት ለምርመራ ይወስድ ኑረዋል። እኛንም እንዲተኮስብን ታሰረን ከቆምንበት ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጠበል አጠገብ ካለው ሸለቆ እስራታችንን አስፈትቶ በአምስት ረድፍ ወደላይኛው መንገድ ለመድረስ ስንሄድ በአካፋ ራሳቸውን የተፈለጡ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ። ምራቄ ደረቀ። በካሚዮኑ ወደ እስር ቤት አስወሰደን። ለጊዜው እስር ቤት ያደረጉት ማዘጋጃ ቤትን ነበር።«ስድስት ኪሎ በሚገኘው የያኔው ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ያሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ለኔፕልስ ልዑል ልደት ክብር ተብሎ በተዘጋጀው መሰናዶ አጋጣሚ፣ በወቅቱ የተፈጠረውን የፋሺስት ጣሊያን ጭፍጨፋ የታዘበው ሀንጋሪያዊው ሐኪም ዶ/ር ላዲስላስ ሳቫ ዓይኑ ያየውንና የታዘበውን በማስታወሻው መግለጹን በጳውሎስ ኞኞ «የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት» መጽሐፍ ላይ እንዲህ ተመልክቷል፡-

«ከዚህ በኋላ በግቢውና በአካባቢው ወዲያውኑ ጅምላ ጭፍጨፋ ተጀመረ። … በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን አንድም በሕይወት የተረፈ ሰው አልነበረም። ቦታው ላይ የተካሄደው የጅምላ ጭፍጨፋ የተሰበሰቡት ሰዎች ዕድሜያቸው የገፋ፣ ዓይነ ሥውራን፣ አካል ጉዳተኞች፣ የኔብጤዎችና ሕፃናትን የያዙ ድሃ እናቶች ስለነበሩ በዚህ ቦታ የተፈጸመው ሰቆቃ ትርጉም የሌለው፣ የሚሰቀጥጥና የሚያሳፍር ነበር።»

**የጭፍጨፋው ተቀዳሚ ዒላማ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በተለይም የጥቁር አንበሳ አባላት ከራስ እምሩ ጋር እጃቸውን ከሰጡ በኋላ በከተማዪቱ ይገኙ ስለነበር በወረንጦ እየተለቀሙ ተረሸኑ። ይህ የምሁራን ጭፍጭፋ አንድ ትውልድ እንዳለ ያጠፋ በመሆኑም በሀገሪቱ የፖለቲካና ምሁራዊ ታሪክ ላይ የማይሽር ቁስል ጥሉ አለፈ**

እርመኛ አርበኞቹ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም በግራዚያኒ ላይ ጥቃት ከፈጸሙ በኋላ በተሽከርካሪው ወደ ፍቼ የወሰዳቸው ስምዖን አደፍርስ ነበር። የፋሺስቶች የግፍ ሰለባ ስለሆነው ስምዖን አደፍርስ በጴጥሮስ ጳውሎስ የካቶሊክ መካነ መቃብር በሚገኘው ሐውልቱ ላይ ገድሉን እንዲህ ጽፎታል። «ወጣቱ አርበኛ ስምዖን (1905-1929) የአብርሃና የሞገስ የልብ ጓደኛ ነበር። ከአደጋውም በኋላ ከአዲስ አበባ ያሸሻቸው በታክሲ መኪናው ነበር። ከዚያም በኋላ ተይዞ ደጃች ውቤ ሠፈር በግራዚያኒ ወህኒ ቤት ማቅቆ አካሉ ከሰውነቱ ውጪ ሆኖ በመርዝ ተገደለ። ዘመዶቹ በድብቅ ቀበሩት።»

አበው«ነውን ለማወቅ ነበርን ጠይቅ፤» ይላሉ። ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ከጥቁር ዓለም ልቃ በነፃነት የኖረችበት በቅኝ ገዢዎች በአካል ያለ መንበርከክዋ ምሥጢር የሚቀዳው ከነበር ታሪኳ ለመሆኑ እነዚያው አበው ብሂሉን ማጣቀሻ አድርገው ያቀርባሉ። ኢትዮጵያ ከ136 ዓመታት በፊት በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመን በዶግአሊ የኢጣሊያ ወራሪ ሠራዊትን በራስ አሉላ ጠቅላይ አዝማችነት የደመሰሰችበት የመጀመሪያው በአውሮፓ ላይ የተገኘ ድል ነበር።

ከዶግአሊ ዘጠኝ ዓመት ቆይታ በኋላ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ግዙፉን የጣሊያን ወራሪ ሠራዊት በዳግማዊ ምኒልክ ጠቅላይ አዝማችነት ዓድዋ ላይ በድል መደምደሙ በተለይ የጥቁር ዓለም መኩሪያ ለመሆን በቅቷል። የ40 ዓመት ቂም የቋጠረው የኢጣሊያ ፋሺስታዊው መንግሥት በ1928 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የፈጸመው ወረራ ከአምስት ዓመት የአርበኞች እርመኛ ትግል በኋላ በድል ተደምድሟል። ይሁን እንጂ በአምስቱ አመት የፋሺስት ወረራ ዘመን ከተፈጸሙት ግፎች አንዱ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈጸመው ነው።

ከፍ ብሎ እንደተመለከተው በፋሽስት ኢጣሊያ ጭፍራ ማርሻል ሮዶልፎ ግራዚያኒ አማካይነት በአዲስ አበባ ከተማ ለሦስት ቀናት በዘለቀው ጭፍጨፋ ሰማዕት ለሆኑት ከ30 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን መታሰቢያ እንዲሆን በአዲስ አበባ ስድስት ኪሎና በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሐውልቶች ቆመዋል። እነዚህን ሰማዕታት ለመዘከር ከ1934 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በብሔራዊ በዓልነት እስከ 1966 ዓ.ም ሲከበር ኖሯል። የኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት (ደርግ) ሥልጣን ከያዘበት 1967 ዓ.ም ወዲህ ግን በመሠረዙ እስካሁን ታስቦ እየዋለ ነው።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ 14ኛ ዓመት የዘውድ በዓላቸውን ሐሙስ ጥቅምት 23 ቀን 1937 ዓ.ም ሲያከብሩ በተመረቀውና ለአርበኞችም የተጋድሎ ሜዳሊያ ባበረከቱበት አዲሱ ሐውልት ግርጌ በግእዝ ቋንቋ የተጻፈው ጽሑፍ ዘመነ ፍዳውን የሚያስታውስ ነው።«ዝንቱ ውእቱ ምዕራፈ አዕጽምቲሆሙ ለብዙኃን ኢትዮጵያውያን እለ ተቀትሉ በግፍዕ በእደዊሆሙ በሕዝበ ኢጣሊያ ፋሽስታውያን አመ ፲ወ፪ ለየካቲት በ፲ወ፱፻፳ወ፱ ዓም …»

ይህ የአፅሞች ማረፊያ በኢጣሊያ ፋሽስታውያን እጅ በግፍ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም የተገደሉ የብዙኃን ኢትዮጵያውያን መታሰቢያ ነው፤ በሚል የሚንደረደረው የሐውልቱ ጽሑፍ አገዳደላቸው በድንጋይ በመወገር፣ በዱላ በመቀጥቀጥ፣ በአካፋ፣ በዶማ በመብረቅ ሐፂን/የብረት መብረቅ (መትረየስ)፣ በየቤታቸው ውስጥ በእሳት በመቃጠል፣ ወዘተ እንደሆነ ይዘረዝራል።

የግፍ አገዳደሉ በተፈጸመ በአራተኛው ዓመት ከብሪታኒያ በድል አድራጊነት የተመለሱት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የነፃነት ምልክት የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ ካቆሙ በኋላ በግፍ የተገደሉትን አፅሞች ከየቦታው እንዲሰበሰቡ ሹማምንቱን በማዘዝ ለዝክረ ነገር እንዲሆንም በቅዱስ ስፍራም መታሰቢያውን አቆሙላቸው። ዝክረ ነገሩ እንደታሰበው ዓመት ታመት በክብር እየዘለቀ እንዳልሆነ የሚናገሩት መምህር መንክር ገብሩ፣ በባሕር ማዶ ያሉ ኢትዮጵያውያን መታሰቢያውን በማክበር ብቻ ሳይወሰኑ የኢጣሊያ መንግሥት ለኢትዮጵያ ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል እየጠየቁ መሆኑ ያስደስታል፤ እኛም የነሱን አርአያ መከተል አለብን፤» ይላሉ። የሮዶልፎ ግራዚያኒ የያኔዋ የፋሺስት ጣሊያን በአምስት ዓመቱ ወረራ ወቅት በዓለም የተከለከለ መርዝ ጋዝ ከአውሮፕላን መወርወርን ጨምሮ በርካታ የጭካኔ ተግባራትን በኢትዮጵያውያን ላይ ፈጽማለች። በአዲስ አበባ እና በደብረሊባኖስ ገዳም የተጨፈጨፉትን ጨምሮ በአምስት ዓመቱ የወረራ ወቅት በብዙ መቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መስዋእት መሆናቸው ይጠቀሳል።

ይሁንና ለዚህ ግፍ፣ ሰቆቃና ጭፍጨፋ የጣሊያን መንግሥት በአደባባይ ይቅርታ መጠየቅ ይቅርና በሥርዓት እውቅና አልሰጠም። በፋሺስት ጣሊያን የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም በአዲስ አበባና በደብረ ሊባኖስ በንጹሐን ላይ ለተፈጸመው ጭፍጨፋ ግፈኞች ለሕግ ስላልቀረቡ፣ ተጸጽተው ይቅርታ ስላልጠየቁና ሀገራቸውም እውቅና ስላልሰጠ፤ ሀገር በቅጡ ያልተጽናናችበትና ጠባሳዋም ያልሻረበት ጥቁር ቀን ነውና፤ መንግሥት ከሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ጋር በመቀናጀት የጣሊያን መንግሥት ለተፈጸመው ግፍ እውቅና እንዲሰጥ፣ ይቅርታ እንዲጠይቅና ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል ከማድረግ ጎን ለጎን በሀገር ውስጥ ደግሞ የሰማዕታት ቀን ታስቦ ከመዋል ይልቅ እንዲከበር በማድረግ ትውልዱ እንዲማርበት ሊያደርግ ይገባዋል ብዬ አምናለሁ።

ሻሎም ! አሜን ።

# ወቅታዊ

# ‹‹ፓርኩን በ2030 የአፍሪካ ዲጂታል ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው››

**አቶ ሄኖክ አህመድ**
**የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ**


ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ

**ማህሌት አብዱል**

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መበልፀግ የላቀ ድርሻ እንዳለው ይታመናል። ኢትዮጵያም በተለይም የምጣኔ ሀብቷን ለማሳደግና በዘርፉ ሰፊ የሥራ እድል ለመፍጠር ያስችላት ዘንድ የተለያዩ የልማት ግቦችን አቅዳ ስተገብር ቆይታለች፡፡ ለዚህም ይረዳት ዘንድ በአፍሪካ ቀዳሚ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማዕከል ይሆናል ያለችውን በ2003 ዓ.ም በ200 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የኢ.ይ.ሲ.ቲ ፓርክ ማቋቋሟ ይታወሳል። የቴክኖሎጂ ዘርፉን የማሳደግ ዓላማ ሰንቆና ለ300 ሺ ሰው የሥራ እድል ይፈጥራል ተብሎ የተቋቋመው ይሄው ፓርክ በተለያዩ ሀገራዊና ውስጣዊ ችግሮች ምክንያት እንደታሰበው ውጤታማ ሳይሆን መቅረቱ ይነገራል፡፡

ይሁንና ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ግን መንግሥት እንደሀገር ካስቀመጣቸው ቁልፍ የልማት መርሀ ግብሮች መካከል የቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ አንዱ በማድረጉ በዘርፍ መነቃቃት እየታየ ነው፡፡ በተለይም ፓርኩ ራሱን ችሎ እንዲቋቋም በማድረግና በመስኩ ላይ ይነሱ የነበሩ የመሰረተ ልማትና መሰል ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣም በዚህና በቀጣይ የልማት ሥራዎች ዙሪያ ከፓርኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሄኖክ አህመድ ጋር ቆይታ አድርጓል እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ፓርኩ መጀመሪያ ሲመሠረት ከያዘው ዋነኛ ዓላማ እና ተልዕኮ አንፃር ውጤታማነቱ እንዴት ይለካል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** እንደሚታወቀው ፓርኩ የተጀመረው ከዛሬ 14 ዓመት በፊት በቀድሞ ኮሙዩኒኬሽን ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እንደፕሮጀክት ተይዞ ነበር፡፡ በደንብ ቁጥር 177 በሚኒስትሮች ምክር ቤት በተቋቋመ ኮርፖሬሽን ስር ሆኖ የተመሰረተው ይህ ፓርክ በወቅቱ በጎሮ ቦሌ ለሚ አካባቢ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማዕከል ኢትዮ አይ.ሲ.ቲ ቪሌጅ በሚል የተቋቋመ ነው፡፡ ነገር ግን ደግሞ ኮርፖሬሽኑ የታሰበው አንድ ፓርክ ብቻ ሳይሆን በርካታ ፓርኮችን እያለማ ለማስተዳደር ተብሎ ነበር፡፡ ከዚያ አንፃር የመጀመሪያ የተባለው ይሄ ፓርክ ሲሆን፤ በወቅቱ የነበረው መሰረታዊ ሃሳብ አንደኛው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ሥራ ጠባቂ ሳይሆን በአይ.ሲ.ቲ ዘርፍ ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ለማበረታታትና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን እንደ ቢሮ፣ ኢንተርኔት፤ መብራትና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ሳይቆራረጡና በአስተማማኝና በተሟላ ሁኔታ በማቅረብ የራሳቸውን ድርጅት እንዲፈጥሩ ያመቻቻል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው የተነሳው በዚህ ዘርፍ ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል የሰው ሀብት ለማፍራት ሲሆን፤ ራሱም ሥራ ይፈጥራል፤ የፈጠረው የሰው ኃይልም ከዚህ እየወጣ ለተለያዩ ድርጅቶች ተቀጥሮ እንዲሰራ ለማድረግ ትልቅ ህልም ሰንቆ ነበር፡፡ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን መሳብ ደግሞ ሶስተኛው ዓላማ ነበር፡፡ በተለይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአይ.ሲ.ቲ ዘርፍ የተሰማሩ ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እውቀታቸውና መዋእለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ለማድረግ የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር ያለመ እንደነበር እሙን ነው፡፡

በዋናነት ደግሞ ለኢንዱስትሪው ብቁ የሆነ የሰው ኃይል የምንፈጥርበት ማዕከል ይሆናል ተብሎ እንደመታሰቡ፤ ይህንን ዓላማ ለማሳካት በወቅቱ ጥናት ተደርጎ ነበር፡፡ ጥናቱን ያሸነፉት ዊፕሮና ሲስኮ የተባሉ ዓለም አቀፍ የህንድ ድርጅቶች ናቸው፡፡ በወቅቱ እነዚህ ድርጅቶች የአዋጭነት ጥናት ሰርተዋል፤ በዚያ መሰረት እንቅስቃሴ ሲደረግ ነበር፡፡ በዚያ እንቅስቃሴም ጥረት ሲደረግ የነበረው የተወሰኑ ድርጅቶች ወደ አይ.ሲ.ቲ ፓርክ እንዲገቡ ነበር ፡፡ ይሁንና እንደተጠበቀው የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሊገቡ አልቻሉም፡፡

የኢትዮ- ቴሌኮም ዋና መስሪያ ቤትም እዚሁ ግቢ ውስጥ እንዲሆን እንቅስቃሴ ሲደረግ ነበር። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች የሕንፃው ግንባታ ተቋርጦ ቆይቷል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ባለበት ሁኔታ ለውጡ መጣና በመንግሥት ውሳኔ ኢንፍርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ኮርፖሬሽን ስር እንዲዞር ተደርጎ ለአምስት ዓመት ያህል በዚያ ሲተዳደር ቆየ፡፡ በዚህ ወቅት የገጠመው ችግር ኮርፖሬሽኑ የሚያስተዳድራቸው ፓርኮችና የአይ.ሲ.ቲ ፓርክ ባህሪ የሚለያይ በመሆኑ እነዚያ ፓርኮች ብዙዎቹ የቀላል ማምረቻ ኢንዱስትሪ ላይ የተሰማሩ በመሆናቸው እንደታሰበው ውጤታማ ሥራ መሥራት አልተቻለም፡፡ ደግሞ ኢንዱስትሪዎቹ ከፓርኩ በተለየ መልኩ በአብዛኛው የሚፈልጉት የጉልበት ሰራተኛ ሲሆን፤ በተጨማሪም የሚቀጥሩት በብዛት መካከለኛ የእውቀትና የልምድ ደረጃ ያላቸውን ነው፡፡ እንደአይ.ሲ.ቲ ያሉ ፓርኮች ግን ከፍተኛ የእውቀት ደረጃ የሚጠይቅ ቴክኖሎጂ ፓርክ በመሆኑ አብሮ ለማስተዳደርም ሆነ ለመምራት አዳጋች ነበር፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ፓርኩን ለየት የሚያደርገው የሥራ እድል መፍጠር ብቻ ሳይሆን ማፍሪያ ኢንኩቤሽን ጭምር ሆኖ የሚያገለግል መሆኑ ነው፡፡ አስቀድሜ እንዳልኩት ወጣቶች ሰልጥነው፤ ራሳቸውን አብቅተው፤ የየራሳቸውን ኩባንያ እየፈጠሩ የሚሄዱበት፤ ቴክኖሎጂ ሽግግር የሚደረግበት፤ ሰዎች የሚሰለጥኑበት፤ ኩባንያዎች አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ድጋፍ የሚደረግበት ማዕከል ነው፡፡ እንደሌሎቹ ፓርኮች ሼድ አናከራይም፤ ምርት የሚመረትበትም አይደለም፡፡ ስለዚህ ይሄ ችግር ስለተፈጠረ መንግሥት እንደገና ፓርኩ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ተጠሪነቱ ሆኖ ግን ደግሞ ራሱን ችሎ እንዲቋቋም ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ በቦርድ እንዲመራ ተደርጎ ነባሩን ተልዕኮ በመያዝ ከአዳዲስ አላማዎች ጋር ራሱን እያስተዳደረ ይገኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ፓርኩ በአዲስ መልክ ከተቋቋመ በኋላ ምን ምን ሥራዎችን አከናውኗል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ በአዲስ መልክ ለመደራጀት የሚያስችሉትን ስራዎች ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ በዚህ ሂደት ፓርኩ ያጋጠመው የመሰረተ ልማት ችግር ነበር፡፡ እንደኢንተርኔት፣ መብራት፣ ውሃ፣ አካባቢው ደግሞ ከአዲስ አበባ ትንሽ ራቅ ስለሚል ትራንስፖርት፣ የምግብ አገልግሎት በአቅራቢያው ያለመኖር የመሳሰሉት ችግር ፈተና ሆነውበት ቆይተዋል። ስለዚህ ለሥራ ምቹ ያልሆኑ ብዙ ችግሮች ነበሩ፤ እነሱን ለማስተካከል ጥረት ሲደረግ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም ወደ ፓርኩ ገብተው ከነበሩት 100 የሚደርሱ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ውስጥ 60 በመቶ የሚሆኑት ጥለው ወጥተዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት የመሰረተ ልማት ችግሩን መቋቋም ባለመቻላቸው ነው፡፡

እንደሚታወሰው ከውጭ የመጣው የቴክኖ ሞባይል መገጣጠሚያ ኩባንያ ብቻ ነበር፡፡ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ችግር አጋጥሞት ነበር፤ ወደ ሙሉ የማምረት አቅም እንዲመጣ ድጋፍ ስናደርግለት ቆይተናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ሌሎች ኩባንያዎችም ገብተዋል፡፡ ለምሳሌ በዳታ ሴንተርና ቢዝነስ ዘርፍ የገቡ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ዳታን እንደአገልግሎት ለማቅረብ የመጡ የውጭ ድርጅቶች አሉ፡፡ ለአብነት ብንጠቅስ ዊንጎ አፍሪካና- ራይክሲዮ የሚባል ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ለራሱም ለውጭም አገልግሎት የሚሰጠው ሳፋሪ ኮም ኢትዮጵያ ድርጅት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ዳታ ሴንተሮች 50 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስት የተደረገባቸው ናቸው። በዚህ ዘርፍ በመሰረተ ልማት ብቻ ይህንን ያህል ኢንቨስትመንት ከዚህ ቀደም አልተደረገም፡፡

ለእነዚህ ድርጅቶች የኃይል አቅርቦት ከአቅራቢያችን ካለ ቅርንጫፍ ጣቢያ 13 ሜጋ ዋት እንዲያገኙ፤ ወደፊት ደግሞ 200 ሜጋ ዋት የኢንተርኔት ኮኔክሽን እስከ 40 ጂቢ ድረስ አስገብተናል፡፡ ሌሎች አገልግሎት ለመስጠት የሚያስቸግሩ ሕንፃዎችን አስተካክለናል፡፡ እኛ ከመጣን ከ 30 በላይ የሚጠጉ ድርጅቶች በፓርኩ ኢንቨስት ለማድረግ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ከዚህ ቀደም የነበሩት 25 ነበሩ፤ ቢሆንም ሁሉም ግን በሥራ ላይ አልነበሩም፡፡ የተወሰኑት ከፓርኩ ውጪ ቢሮዋቸውን አድርገው የሚሰሩ አሉ፤ ይሁንና እስካሁን ድረስ አድራሻቸውን ያላገኘናቸው አሉ። ቀሪዎቹ አድርሻቸው ይታወቃል፤ ‹‹የመሰረተ ልማት ችግር ስላለ ዘግተን ወጥተናል›› ያሉትን እንዲመለሱ ጥረት እያደረግን ነው፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ጀኔሬተርና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን አሟልተው ለመስራት ጥረት እያደረጉ ነበር፡፡

ሕንፃውን ለረጅም ዓመታት ተከራይተው የጠፉና መመለስ ያልቻሉትን ድርጅቶች ወደ ህግ እንልከዋለን። ምክንያቱም ሕንፃው የተሰጣቸው እንዲያለሙበት በመሆኑ ለመስራት ፍቃደኛ ካልሆኑ በኮሜቴ በያዙት ቦታ አስወጥተን ለሚያመርት ለሌላ ድርጅት እናከራየዋለን። በተጨማሪም መሬት ለ60 ዓመት በሊዝ ለማከራይት የተሰጠን፤ ከዚያ 60 ዓመት ውስጥ 16 ዓመቱ አልፏል። የሚቀረው 44 ዓመት ነው፤ በእነዚህ ዓመታት የሚጠበቀው ለአገልግሎት ሰብ-ሊዝ ሕንፃ ገንብተው እዚሁ አይ.ሲ.ቲ ባርክ ውስጥ እንዲሰሩ ነው፡፡

አካባቢው ለኢንቨስተሮች ሳቢ እንዲሆንና በዋናነት ለሀገሪቱ ቴክኖሎጂ አቅም በሀገር በቀል ድርጅቶች ለመጠቀም እንዲያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ እየተሠራ ነው፡፡ ስለዚህ ፓርኩ በ2030 የአፍሪካ ዲጂታል ማዕከል ለማድረግ እየተሰራ ነው። በአሁኑ ወቅት እየተንቀሳቀሰ ያለው ይህንን ራዕይ ይዞ ነው ፡፡ ይህም ሲባል በ2030 ከውጭና ከሀገር ውስጥ ድርጅቶችና ከግለሰቦች የሥራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ወደ ፓርኩ ለማስገባት ሥራዎች ይሠራሉ፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ምርቶቻውንና አገልግሎታቸውን ይዘው ወደገበያ እንዲወጡ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ ዓላማችን የዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ሆነው ከሀገር ውስጥ አልፈው ወደ ውጭ መላክ እንዲችሉና የውጭ ምንዛሬ እንዲያስገቡ ለማድረግ ነው፡፡

በዋናነት ግን ቅድሚያ ትኩረት የሰጠነው አቅማችንን በማጎልበት የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ማርካት ለሚያስችል ሥራ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ወጣቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀምጠው በኢንተርኔት አማካኝነት ዓለም አቀፍ ሥራ የሚሰሩበት እድል በማመቻቸት አገልግሎትን ኤክስፖርት በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ለማስገባት የሚያስችል ሥራ ለመስራት ዝግጅት አድርገናል፡፡ እዚህ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችን ጋብዘን ወደ ፓርክ እያስገባን ነው፡፡ ትልቅ ትኩረት የሰጠነው ከውጭ ምንዛሬ ማስገባት አንፃር ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሥራ እድል ይፈጥራል ተብሎ የታሰበው ነው፡፡

ሁለተኛው በአይ ቲ ዘርፍ የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች አቅማቸውን የማሳደግ ሥራ ይሰራል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ በዘርፉ ለሚገኝ ማንኛውም እውቀት ለውጭ ድርጅቶች የምናወጣውን ወጪ ለመቀነስ የሀገር ውስጥ አቅምን ለማጎልበት ጥረት ይደረጋል፡፡ በዋናነትም ኢትዮጵያ ውስጥ በውጭ ኩባንያዎች በሚሰሩ ማንኛውም ፕሮጀክቶች አማካኝነት የእውቀት ሽግግር እንዲመጣ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው፡፡

የኤሌክትሮኒክስ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን ማልማት ደግሞ ሌላኛው የትኩረት መስካችን ነው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ መቶ በመቶ በሚባል ደረጃ ከኤርፎን ጀምሮ የማኑፋክቸሪንግ ውጤቶች የምታስገባው ከውጭ ነው፡፡ ለእነዚህ ቁሳቁሶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የምታውሉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ ለሌላ ልማት መዋል የሚገባው ሀብት እየወጣ ይገኛል፡፡ ይህም ምጣኔ ሀብቷን በሚፈለገው ደረጃ እንዳታሳድግ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም ይህንን ከውጭ የሚገባው የአይሲቲና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን በተወሰነ ደረጃ ለማስቀረት የሚያስችል ሥራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃርም ፓርኩ በረጅም ጊዜ እቅዱ ይፈፅማል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቀድሞ በነበረው የተቋሙ**

**ወደ ገጽ 8 ዞሯል**

# ወቅታዊ

# ‹‹ፓርኩን በ2030 የአፍሪካ ዲጂታል...

ከገጽ 7 የዞረ



**አደረጃጀት ኢትዮ- ቴሌኮም ፓርኩ ውስጥ እየገነባ የነበረውን የሕንፃ ግንባታ ያቋረጠበት አብይ ምክንያት ምን ነበር? በቀጣይስ ምን ታስቧል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** እንደተባለው ግንባታው በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ወጪው ከእጥፍ በላይ ጨምሮ ተቋርጧል። ኮንትራቱ የተሰጠው ለውጭ ድርጅት በመሆኑ የዶላር ጥያቄ ነበረበት፡፡ በመሆኑም መረጃው ያለኝ ይህንን ወጪ መሸከም የሚያስችል በጀት ባለመኖሩ ግንባታውን ማቋረጥ ግድ ይላል። አሁን ግን ለመስራት ዝግጁ ነን ብለው ኮንትራት እየተፈራረምን ነው፡፡

በመሰረቱ ቀድሞም ቢሆን ከፓርኩ ጋር የሊዝ ኮንትራት አልተፈራረምንም ነበር፡፡ በመሆኑም የሊዝ ኮንትራቱን ለመፈረም የህግ ጉዳዮችን ጨርሰናል። እንግዲህ የሚጠበቀው ከዚህ በፊት የተሰጠው የቻይና ኮንስትራክሽን ኩባንያ ነበር፤ ኩባንያው ለመቀጠል በተደረገው ጥረት መሰረት ሕንፃው ይጠናቀቃል፤ ነገር ግን የታወቀው ከተያዘለት በጀት እጥፍ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑ ከዚህ የቻይና ድርጅት ጋር ድርድር እየተደረገ ነው፡፡ ይሄ ድርድር በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንዲገባ እኛም እየተከታተልን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ኢትዮ ቴሌኮም ግንባታውን አጠናቆ ወደ ሥራ ሲገባ ምን ምን ነገሮች ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል?**

አቶ ሄኖክ፡- የአይ.ሲ.ቲ ኢንዱስትሪ አንዱ ምሰሶ ቴሌኮም ነው፡፡ በዋናነት ኢትዮ ቴልኮም ለአይ.ሲ.ቲ ኢንዱስትሪ የሚያደርገው ድጋፍ መካከል የአይ.ሲ.ቲ መሰረተ ልማት መዘርጋት ተጠቃሽ ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮ ቴሌኮም ወደ ፓርኩ መምጣት ተከትሎ ሌሎች ከእርሱ ጋር የሚሰሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎችም ወደ እዚህ ይሳባሉ ማለት ነው። ይህም የፓርኩን አቅም ከፍ ለማድረግ ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ወደ ፓርኩ ስመግባት ጥያቄ አቅርበው የገቡ አዳዲስ ድርጅቶች በምን በምን መስክ እየሠሩ ነው?**

**አቶ ሄኖክ፡-** ወደ አይ.ሲ.ቲ ፓርክ ለመግባት ሶስት ዘርፎች ያሉ ሲሆን፤ ተጨማሪ አምስት የልማት የትኩረት አቅጣጫዎች አሉ፡፡ እነዚህ ዘርፎችም አስቀድሜ እንደገለፅኩት ቢዝነስ ፕሮሰስ አውትሶርሲንግ (ቢፒኦ)፤ አይ.ሲ.ቲ ሰርቪስ ፤ ኤሌክትሮኒክስ ዘርፎች ናቸው። ቢፒኦ ሲባል ሀገር ውስጥ ሆኖ የአይ.ሲ.ቲ አገልግሎት ለውጭ ሀገራት መሸጥ ማለት ነው፡፡ የአይ.ሲ.ቲ መሰረተ ልማት፤ ሶፍትዌር መሸጥ፤ ማማከርና የመሳሰሉት ሥራዎች የሚከናወንበት ነው፡፡ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችም የሚያመርቱም ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ አዳዲሶቹ ኩባንያዎች በእነዚህ ሶስት ዘርፎች ውስጥ መርጠው መሰማራት የሚችሉበት እድል አለ፡፡

ሌላው ድርጅቶቹ ለእነዚህ ሥራዎች አስቻይ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ሲባል በተጠቀሱት ዘርፎች ላይ የሚያቀርበው ዕቅድ (ፕሮፖዛል) በተለይ የሥራ እድል ከመፍጠር አንፃር ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ በተጨማሪም ብቁ የሰው ኃይል በመፍጠር፤ ከውጭ የሚገባውን ከመተካት እና ወደ ውጭ በመላክ ረገድ፤ በቴክኖሎጂ ሽግግርና አጠቃላይ በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው አስተዋፅኦ የሚያሳይ ሥራ ይዘው ከቀረቡ በፓርኩ ውስጥ ከሚገኙ ሕንፃዎች ወይም መሬት በሊዝ ተከራይተው መስራት ይችላሉ፡፡

በዚህ ረገድ የሊዝ ዋጋ በጣም ከፍ ያለ በመሆኑ ማሻሻያ ሰርተን ወደ ቦርድ ልከናል፡፡ ማሻሻያው እስኪተገበር ድረስ በነበረው እየሰሩ፤ ፀድቆ ወደ ትግበራ ሲመጣ ደግሞ በተሻሻለው ተመን እንደሚሰሩ ውላቸው ላይ ተካቷል፡፡ በዚህ መሰረት አዳዲስ የገቡት ድርጅቶች በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሥራ እንደሚጀምሩ ይጠበቃል፡፡ ከዚያ በኋላ ፓርኩ የተሰጣቸውን ተልዕኮ ያሳካሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይ ከውጭ የሚገባውን ምርት በመተካት ሀገሪቱ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማዳንና አገልግሎትን በመሸጥ ለሀገር ጥቅም እንዲያስገቡ ይታሰባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ፓርኩ ሲቋቋም በዋናነት ሶፍትዌር በመገንባት ረገድ ትልቅ ተስፋ ተጥሎበት ነበር፤ አሁን ላይ ያ ተስፋ ምን ላይ ደረሰ?**

**አቶ ሄኖክ፡-** እንደተባለው ፓርኩ ከሚሰጣቸው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ ሶፍትዌር ልማት ነው፡፡ ስለዚህ በዋናነት ከውጭ የምናስገባውን ሶፍትዌር እዚሁ ማስቀረት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የመጀመሪያና ዋነኛው ትኩረታችንም ሶፍትዌር ማልማት ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ሃርድ ዌር የምንለውና የአይ.ሲ.ቲ ግብዓትን ማምረት ላይ ብዙ የሚቀረን በመሆኑ ነው፡፡ ግን ደግሞ ከውጭ የሚገባውን በአምስት ዓመታት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ለመተካት አቅደናል፡፡ በሶፍትዌር ልማት ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ የምናሳካው በመሆኑ ትኩረት አድርገን እየሰራንበት ነው፡፡ አሁን ካሉት ድርጅቶች ውስጥ የተወሰኑት ወደዚህ ልማት ዘርፍ የገቡ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀደም ገብተው ያለሙ አሉ፡፡ ለምሳሌ ከገባ አስር ዓመት የሆነው ድርጅት አለ፤ በእነዚህ ዓመታት ይሄ ድርጅት ሲሰራ የነበረው ሶፍትዌር ልማት ላይ ነው፡፡ ከሰራቸው ሥራዎች ውስጥ የመሬት ማኔጅመንት ላይ የካዳስተር ሥራ፤ ሴፋቲኔት፣ ጤና ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሶፍትዌር የሰራው ይሄ ድርጅት ነው፡፡ በተጨማሪም 3ሚሊዮን የማይክሮ ፋይናንስ ተበዳሪዎችን ወደ ብሔራዊ ዲጅታል መታወቂያ ለማስገባት ፕሮጀክት አሸንፎ እየሰራ ነው፡፡ ስማቸው ጎልቶ አይውጣ እንጂ ሌሎችም አሉ፤ ከፊሎቹ ኔትወርክ ላይ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ አሉ፡፡

ያም ቢሆን ግን ፓርኩ ሲቋቋም ይዞት ከተነሳው ራዕይ አንፃር አሁን እየተሰራ ያለው በቂ የሚባል አይደለም። እንደሚታወሰው ደግሞ በአስር ዓመት ውስጥ 300 ሺ ሰው ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል። አሁን ላይ መፍጠር የተቻለው የሥራ እድል ሁለት ሺ እንኳን አይሞላም።

ስለዚህ ፓርኩ አንዱ አልተሳካለትም የምንለው የትኩረት ላአቅጣጫ ከሥራ እድል ፈጠራ አንፃር ነው። አሁን የመንግሥት ውሳኔ ከኢንዱስትሪያል ፓርክ ኮርፖሬሽን ራሱን ችሎ እንዲደራጅ የተፈለገበት ዋነኛ ዓላማ ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግና እንደታለመው ከፍተኛ የሥራ እድል ለመፍጠር ነው፡፡ በአሁኑ ያለውን ከ1ሺህ 200 የሥራ እድል በሶስት ዓመታት ውስጥ አስር ሺ ለማድረስ እንዲያገኙ አቅደን እየሰራን ነው፡፡ እንደተባለው በአስር ዓመት ውስጥ 300ሺውን ለማሳካት እንተጋለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት በ2025 ዲጂታል ኢትዮጵያን ለመፍጠር እየሠራ ላለው ሥራ የፓርኩ ሚና ምንድን ነው?**

**አቶ ሄኖክ፡-** አስቀድሜ የጠቀስኳቸው ሥራዎች በሙሉ የዲጂታል 2025 ስትራቴጂ ውጤቶች ናቸው። ስትራቴጂው አንዱ ያስቀመጠው ቢፒኦ ነው፤ በዚህም የሥራ እድል መፍጠር፤ አገልግሎትን ወደ ውጭ ልኮ የውጭ ምንዛሬ ማምጣት ነው፡፡ ሁለተኛው የሰው ኃይል ልማት ነው፡፡ ሁለተኛው በስትራቴጂው ጎልቶ የወጣው የሰው ኃይል ልማት ነው፤ የሰው ኃይሉን በስፋት ማሰልጠንና ወደ ሥራ ማስገባት ነው፡፡ ሶስተኛው ኢትዮጵያን በቴክኖሎጂ አቅም ማሳደግ ነው፡፡ አራተኛው አዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎችን የተመቻቸ ሁኔታ በማምጣት ወደ ልማት እንዲገቡ ማድረግ ነው፡፡ ሌላኛው የቴክኖሎጂ ሽግግር ማምጣት ነው፡፡ እንደ አጠቃላይ ፖሊሲውን ለማስፈፀም የተቋቋመ ድርጅት እንደመሆኑ ኃላፊነቱ ትልቅ ነው ማለት እንችላለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ፓርኩ ለሀገር የውጭ ምንዛሪን በማስገባት ረገድ ምን አይነት ሚና እየተጫወተ ነው?**

**አቶ ሄኖክ፡-** አስቀድሜ እንደገለፅኩት አሁን ላይ ፓርኩ በአዲስ መልክ እየተደራጀ እንደመሆኑ በስፋት የሚጠቀስ ገቢ እያስገኘ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለጊዜው ወደ ውጭ መላክ የምንችለው የሰው እውቀትን ብቻ ነው፤ ወጣቶች እዚህ ሆነው ሥራ እየሠሩ የውጭ ምንዛሪ ለሀገራቸው እንዲያስገቡ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረግን ነው፡፡ በመካከለኛ ጊዜ እቅዳችን ግን ሶፍት ዌር በስፋት በማልማት ሀገርን ተጠቃሚ ለማድረግ ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው፡፡ በረጅም ጊዜ ደግሞ ኤሌክትሮኒክስ አምርተን ከእኛ አልፈን የአፍሪካን ገበያ የመቆጣጠር ዓላማ አለን፡፡

ለዚህ ደግሞ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት የፈረመች በመሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሆኖም ወደፊት የሁሉም የአፍሪካ ሀገራት ምርት እዚህ ሀገር ገበያ ላይ እኩል የሚስተናገድበት ሁኔታ ስለሚፈጠር ከወዲሁ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል። ደግሞም ኢትዮጵያ ካላት ሕዝብ ቁጥር አኳያ አብዛኞቹ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ገበያ ይፈልጉታል፡፡ ያኔ ተወዳዳሪ መሆን ካልቻልን ከባድ ይሆናል፡፡ እየሰራን ያለነው በሚቀጥለው አምስት ዓመት ውስጥ ይህንን አቅም መገንባት አለብን ብለን ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ኩባንያዎች አቅም እንዲፈጥሩ ማገዝ ያስፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት ከአምስቱ ምሰሶዎች አንዱ ቴክኖሎጂን አንዱ ማድረጉ ለዘርፍም ሆነ ለፓርኩ ሥራ ምን አስተዋፅኦ ይኖረዋል?**

**አቶ ሄኖክ፡-** የዘረዘርናቸውን የልማት መርሀ ግብሮች ለማሳካት የመንግሥት ትኩረት ወሳኝ ነው። አንድ ተቋም የሀገሪቱ ቴክኖሎጂ አቅም እንዲሆን ለማድረግ የመንግሥት ድጋፍ ያስፈልጋል፡፡ ደግሞም ሁለት መቶ ሄክታር መሬት አዲስ አበባ ውስጥ አጥሮ ማስቀመጥ ቀላል ነገር አይደለም። ከዚያ ይጀምርና ይህ ቦታ እንደ መብራት፣ ቴሌ ፣ ውሃ፣ መንገድና መሰል በመሰረተ ልማትና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሕንፃዎችን እንዲሞላ የማድረጉ ኃላፊነት ነው፡፡ ስለዚህ የመንግሥት የተመረጠ የልማት መስክ ባይሆን ኖሮ ፓርኩ ራሱ እውን መሆን ባልቻለ ነበር፡፡

አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ ሀገሪቱም ሆነ ሕዝቡ ከዚህ ተቋም ምን ይጠብቅ?

አቶ ሄኖክ፡- ፓርኩ አንዱ የገጠመው ነገር የመሬትም ሆነ የሕንፃ ሊዝ ዋጋ ውድ መሆን ነው፡፡ በተጠናው ጥናት መሰረት ለሀገር ውስጥ ቀርቶ ለውጭ ድርጅቶችም ጭምር ውድ ነው፡፡ በተለይ የማምረቻ ኢንዱስትሪን ለመሳብ የሚያስችል አይደለም፡፡ ለምሳሌ ቴክኖ ድርጅት እያመረተ ያለው ከጠቅላላ አቅሙ ከግማሽ በታች ነው። መሠረታዊ ችግሩ የዶላር እጥረት ነው፡፡ ሌላው ፓርኩ አጥር የሌለው በመሆኑ የደህንነት ጉዳይ ስጋት አለበት። ምክንያቱም የመሬት ወረራ ያጋጠመው በመሆኑ ነው። መንግሥት ከከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች የተሰጠንን ትኩረት ያህል ተቋሞችም ሆነ ኃላፊዎች ሙሉ ትኩረት ሰጥተውታል ብዬ አላምንም፡፡ በእርግጥ አንዳንዱ ትኩረት የማይሰጠው ከመረጃ እጥረት የተነሳ ነው፤ ሌላው ደግሞ ካለመናበብ የሚመነጭ ችግር ነው፡፡ በአጠቃላይ ግን ይህ ፓርክ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖሩን ጭምር የማያውቅም አለ፡፡ በመሆኑም እዚህ ፓርክ ውስጥ ያለው ሀገራዊ አቅም ሊታወቅና ለስራው ስኬት መደገፍ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

በዋናነት ፓርኩ በቀጣይ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱን በመጠቀም የታለመለትን ግብ ለማሳካት መትጋት ይጠበቅበታል፡፡ ይህም ግቢውን ለሥራም ሆነ ለኢንቨስትመንት ሳቢና ምቹ ከማድረግ ይጀምራል። ፀጥታውን ማስጠበቅና ለኩባንያዎቹ የሚያስፈልገውን አገልግሎት መስጠት አለብን፡፡ ለምሳሌ ከከተማ ወጣ ያለ በመሆኑ የትራንስፖርት፣ የምግብ አገልግሎት መስጠት አንዱ ሥራ ነው፡፡ እነዚህን ሥራዎች ለማከናወን ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት አለብን፡፡ ኃላፊነቱን ስንረከብ የተነሳነው ከዜሮ ነው፤ ግን አሁን ላይ ኦፕሬሽናል የሆኑ ሥራዎችን እየሰራ ያለው ሙሉ ለሙሉ ራሱን ችሎ ነው፡፡ ግን ደግሞ ትልልቅና ሰፊ የሰው ኃይል የሚፈጥሩ ኩባንያዎችን የመፍጠር ራዕዩን ለማሳካት ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስ ድጋፍ ያስፈልገዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ ሀገር የሚኮራበት የአይሲቲ ኩባንያ የመፍጠር ሂደቱ አሁንም ርብርብ ይሻል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ሄኖክ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የወላይታና አካባቢዋ ሠላም - ለኢንቨስትመንት ምቹነት

አስቴር ኤልያስ

ሠላም የሁሉም ነገር መሠረት ነው፡፡ ሠላም ካለ ወጥቶ መግባት፣ ዘርቶ መቃምና ወልዶ መሳም ይቻላል። አለፍ ሲልም ለኢንቨስትመንት እድገት ሠላም ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ከሰሞኑ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን በነበረው ቆይታ የአካባቢው ሠላም ለኢንቨስትመንት ዕድገት እያበረከተ ያለውን አስተዋፅዖ መታዘብ ችሏል፡፡

የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ በአካባቢው ያለውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አበረታች መሆኑን ሲገልጹ፣ ሥራ አጥነትን ከመቀነስ አኳያ የግሉ ዘርፍ ሰፊ ድርሻ አለው፡፡ ለዚህ ደግሞ ኢንቨስትመንትን መሳብ ትክክለኛው አማራጭ ነው። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያም የተለያዩ ዘርፍ ያላቸውን ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ ላይ ትገኛለች፡፡

እንደ ወላይታ ዞንም ያለው ሁኔታ ይህንኑ የሚያሳይ ነው፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት 53 ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ችለዋል፡፡ ፕሮጀክቶቹ ያስመዘገቡት ጠቅላላ ካፒታልም ሦስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን፣ 680 ሚሊዮን 185 ሺ 901 ብር ሲሆን፣ እነዚህ ባለሀብቶች ከመካከልም ወደ ሥራ የገቡና በሂደት ላይ ያሉ ይገኙበታል፡፡

በዞኑ እየተከናወነ ያለውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ካለፈው ዓመት የኢንቨስትመንት ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም ጨምሯል፡፡ ለአብነት ያህል በገጠር እርሻም፣ በከተማ አገልግሎት ዘርፍ፣ እንዲሁም በመካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጭምር መሻሻል አሳይቷል፡፡ እንደዞን ሲታይ ይህ ትልቅ ለውጥ ነው፡፡ ለዚህም የክልል አደረጃጀት ጥያቄ ምላሽ ማግኘቱ አንዱ ምክንያት እንደሆነ አቶ ሳሙኤል ይናገራሉ፡፡ ከክልል ጥያቄ ጋር ተያይዞ ወላይታ ሶዶ የአስተዳደርና የፖለቲካ ማዕከል ሆናለች፡፡ በመሆኑም አሁን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ በእጅጉ የተረጋጋ ነው የሚሉት አቶ ሳሙኤል፣ በአካባቢው የተፈጠረው ሠላም አስተማማኝና ለኢንቨስትመንት ዕድገት ምቹ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በተለይም ለዲያስፖራው፣ ለሀገር ውስጡና ለውጭ አገር ባለሀብት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ከተመዘገበው ካፒታልም ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው የዲያስፖራው ማኅበረሰብ ነው፡፡ ዲያስፖራው ከተሠማራባቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ውስጥ የሆቴል ቱሪዝም፣ የማኅበራዊ አገልግሎትና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በማኑፋክቸሪንግ አግሮፕሮሰሲንግ ላይ እንዲሠማሩም ዘርፎች ተለይተውና የቢዝነስ አዋጭነታቸው ታይቶ እንዲገባባቸው እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

እርሳቸው እንዳሉት፣ ከኢንቨስትመንት ፕሮጀክት አፈጻጸም ጋር ተያይዞ መሬት ወስደው አጥረው የተቀመጡ አካላት ተለይተው 19 በሚደርሱ ፕሮጀክቶች ላይ ከባድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል፡፡ በቀጣይም በአጭር ጊዜ ውስጥ የማያለሙ ከሆነ የመቀማት እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፡፡ መሬትን ለኢንቨስትመንት ልማት መስጠት ብቻ ሳይሆን ውጤታማ መሆናቸውም በአግባቡ የሚገመገም እንደሆነና የገበያው ሁኔታ ምን ያህል ነው የሚለው እንደሚታይ አመላክተዋል፡፡

ሌሎች ባለሀብቶችም በተረከቡት ቦታ በአፋጣኝ ማልማት እንደሚጠበቅባቸው አቅጣጫ መቀመጡን ጠቅሰው፣ ለኢንቨስትመንት ፍሰቱ መሠረተ ልማት ወሳኝ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በዞኑ እየተከናወነ ያለው የመንገድ ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ አያይዘውም በዞኑ ከፍተኛ የሆነ የሥራ አጥ ቁጥር ስለመኖሩ ያነሱት አቶ ሳሙኤል፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ኢንቨስትመንት ወደ ዞኑ መሳብ ወሳኝ ነው፡፡ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ደግሞ ሠላምና መልካም አስተዳደር ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው ይላሉ፡፡

‹‹ከሠላምና ጸጥታ እንዲሁም ከመልካም አስተዳደር አኳያ የወላይታ ዞን ለሌሎች አካባቢዎች አንጻር ተሞክሮ መሆን የሚችል ነው›› ያሉት አቶ ሳሙኤል፣ በዞኑ የሚገኙ ቀበሌዎች ከወንጀል ስጋት ነፃ በመሆናቸው፣ የትኛውም አካል ከአንድ ስፍራ ወደሌላ ስፍራ በሠላም መንቀሳቀስና መሥራት ይችላል፡፡ ከዚህ አኳያ በዞኑ ወደየትኛውም አቅጣጫ ቢኬድ ዝርፊያም ሆነ ንጥቂያ የሌለበት መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል ብለዋል፡፡


አቶ ሳሙኤል ፎላ


አቶ ፍሬሕይወት ወልደመስቀል

**ከተማዋ ለኑሮ ምቹ የሆነችና የአየር ፀባይዋም መልካም የሚባል መሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ነዋሪዎቿ እጅግ ሥራ ወዳድና እንግዳ ተቀባይ መሆናቸው እንዲሁም በርካታ የተማረና አምራች ዜጋም የሚገኝባት መሆኗም ተመራጭ ያደርጋታል**

ይህም ከሕዝቡና ከፀጥታ መዋቅሩ ጋር ውይይት በማድረግ የመጣ ውጤት ነው መሆኑን በመግለጽ፣ ከሦስት ዓመት በፊት ወላይታ በተለይ ከክልል ጥያቄ ጋር ተያይዞ ፈተናዎች የበዙበት እንደነበረ አስታውሰዋል፡፡ ባለፉት ጥቂት ጊዜያት በተደረገው ውይይትና ምክክር ሕዝቡ ለሠላም ያለውን ቁርጠኝነት ማሳየት ጀምሯል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ዞኑን ከዚህ በበለጠ የሠላም ተምሳሌት ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞም በዞኑ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ እየተሠራ ነው፡፡ አገልግሎት ፈላጊው አካል ያለምንም እንግልት ይስተናገድ ዘንድም እየተሠራ ነው። የተቋማት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ቀልጣፋ እንዲሆንና ጊዜን በአግባቡ መጠቀም እንዲያስችል ትልቅ ሥራ በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም ተቋማትን ከሚመሩ አካላት ጋር ሰፊ ወይይት በማካሔድ መግባባትም መፍጠር ተችሏል፡፡

ከዚህ ቀደም ሕዝቡ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከሚማረርባቸው አንዱ ተቋም ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ነበር፡፡ በዚህ ተቋም በተለይ ከመሬት ጋር እና ሕገ ወጥነት ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮች ነበሩ፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ያንን ችግር ነቅሰን አውጥተን በችግሮቹ ዙሪያ እየሠራን እንገኛለን ብለዋል፡፡

የሶዶ ከተማ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ዩኒት አስተባባሪ አቶ ፍሬሕይወት ወልደመስቀል በበኩላቸው፣ የሶዶ ከተማ አሁን ባለው እንቅስቃሴ ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ፍላጎትና እንቅስቃሴ የሚስተዋልበት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ የልማቱ ሥራ ቀንና ሌሊት መካሔዱን ጠቅሰው፣ ይህን ለመሥራት ከሁሉ በላይ የከተማዋን ሠላም ለማረጋገጥ እየተሠራ ያለው ሥራ ጠንካራ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

ለኢንቨስትመንትና ለሌሎች የልማት ሥራዎች ሠላም ወሳኝ መሆኑን በመጥቀስ፣ ከዚህ የተነሳ ከሁሉ በላይ መቅደም ያለበት ሠላምን ማስፈን ስለሆነ ሠላምን የማስፈኑ ተግባር የፀጥታውን ሁኔታ ለሚመራ አካል ብቻ የሚተው አለመሆኑንና ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበት ነው ይላሉ፡፡

እንደ አቶ ፍሬሕይወት ገለጻ፣ ሁሉም ለሠላም መስፈን የድርሻውን ሲወጣ ኢንቨስትመንቱ የተፈለገውን ያህል ርቀት መሄድ ይችላል፡፡ የሶዶ ከተማ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሜትሮፖሊታን ደረጃ ለማድረስ ታልሞ እየተሠራ በመሆኑ ከተማዋ በዚህ አጋጣሚ ያላትን ፀጋ ልትጠቀምበት ያስፈልጋል፡፡ ምቹ አጋጣሚዎቿም ከተማዋ ሰባት መውጫ እና መግቢያ በሮች ያሏት መሆኑ አንዱ ሲሆን፣ በሰባቱም የመውጫ እና መግቢያ በሮች የንግድ እንቅስቃሴዎች አሉ፡፡ ከዚህ አኳያ ከተማዋ የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚደረጉባት ነውና ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው ይላሉ፡፡ ሌላው ከተማዋ ለኑሮ ምቹ የሆነችና የአየር ፀባይዋም መልካም የሚባል መሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ነዋሪዎቿ እጅግ ሥራ ወዳድና እንግዳ ተቀባይ መሆናቸው እንዲሁም በርካታ የተማረና አምራች ዜጋም የሚገኝባት መሆኗም ተመራጭ ያደርጋታል ብለዋል፡፡ የከተማዋ ነዋሪዎች ከሌሎች ጋር አብሮ መኖርንም ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው ወደ ወላይታ የሚመጡ ኢንቨስተሮች በፍጹም አይከስሩም፣ ይልቁኑ በብዙ ያተርፉበታል ነው ያሉት፡፡

አቶ ፍሬሕይወት እንደሚሉት፣ ባለፉት ስድስት ወራት የነበረው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ሰፊ ልዩነት አለው፡፡ በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት ወደ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ያስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እንዲያገኙ የመጀመሪያ ደረጃ የሆነውን የከተማውን ውሳኔ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ በዚህም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እንዲሁም ሰፊ የሆነ የሥራ አጥ ቁጥርን ይቀንሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በአሁኑ ወቅት ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ ወደ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን፣ የስድስት ወር አፈጻጸም አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ያስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነሱም በዋናነት በማኑፋክቸሪንግ፣ በአገልግሎትና በከተማ ግብርና ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ፍሰቱም በማኑፋክቸሪንግና በአገልግሎት ዘርፍ በርካታ ናቸው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት ማኑፋክቸሪንግ በርካታ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል በመሆኑ ነው፡፡

በአገልግሎት ዘርፉ ሲታይ በርካታ ንዑሳን ዘርፎችን በውስጡ ያካተተ ነው፡፡ ለምሳሌ የሆቴል ቱሪዝም በዚሁ ዘርፍ የሚገኝ ነው፡፡ ለአብነት በሶዶ ከተማ በርካታ የሕክምና ተቋማት አሉ፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ደረጃቸውን በከፍተኛ ሁኔታ የጠበቁ ሆስፒታሎች እየተገነቡና የገቡበትም ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይሁንና አሁንም ለዚህ ዘርፍ አይበቃንም ብለን ስለምናስብ በብዛትና በጥራት እንዲሠራ ትኩረት ሰጥተን እየተንቀሳቀስን ነው ብለዋል፡፡

ከሆቴል ዘርፍ ጋር ተያይዞ ሪዞርቶችና ሎጆች ለአካባቢያችን ያስፈልጉናል የሚሉት አቶ ፍሬሕይወት፣ ብዙ የእንግዳ ማረፊያዎችም አስፈላጊ እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ የወላይታ ሶዶ ከተማ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የፖለቲካና የርዕሰ መስተዳድር መቀመጫ መሆኗን በመጥቀስ ይህ ደግሞ ለከተማዋ ትልቅ አጋጣሚ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በከተማዋ በቀጣይም ቢሆን በርካታ ጉባኤዎች የሚካሔዱ መሆናቸውን በመግለጽ፣ ይህን ፍላጎት የሚመጥን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መካሄድ ስላለበት በእነዚህ ዘርፎች በስፋት እየተሠራ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

ኢንቨስት ለማድረግ ለሚመጡ አካላት ከተማዋ የተሟላ አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ የመጀመሪያው ሥራ ነው፡፡ ከዚህም መካከል ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሠላም የተረጋገጠበት ከተማ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ላይ ከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴው ሰፋ ባለ መልክ የተለያዩ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለባለሀብቱ ማቅረብ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዋናነት እነዚህን አማራጮች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ሥራ ወዳዱን የወላይታ እና አካባቢውን ሕዝብ በማቀናጀት ለኢንቨስትመንት ሥራዎች ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር ከተማዋ 24 ሰዓት የመብራት እና የውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ ናት፡፡ በተጨማሪም የአራተኛው ትውልድ የኤል.ቲ.ኢ ኔትዎርክ ሽፋንም ያላት ከተማ ናት፡፡ ስለዚህ ባለሀብቶቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ባሉበት ቦታ ሆነው ንግዶቻቸውን ከሀገር ውጭ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ማድረግ የሚያስችላቸው ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሯል፡፡ እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም ኢንቨስት እንዲያደርጉ ባለሀብቶችን ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር የመሳብ ሥራ ከተማዋ ቀጥላለች፡፡ ከዚህ የተነሳም በቁጥር በርከት ያሉ ባለሀብቶች በሶዶ ከተማ ኢንቨስት ለማድረግ ጥያቄ እያቀረቡ ነው፡፡ ይህ ፍሰት ሊኖር የቻለው ባለሙያ ምቹ አጋጣሚ ሲሆን፣ በተለይ በሠላሟ፣ ባላት ሥራ ወዳድ ዜጋ እና የተማረና አምራች ዜጋ በአካባቢው በመኖሩ ነው፡፡ ይህ ሥራ ግን አሁንም የሚበቃ አይደለም፡፡ አሁንም በስፋት ታቅዶ በመሠራት ላይ ይገኛል፡፡

ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከተማ አስተዳደሩ ከሶዶ ከተማ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ጽሕፈት ቤት እና ከኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ዩኒት ጋር በቅንጅት ይሠራል፡፡ በሦስቱም ዘርፎች (ማኑፋክቸሪንግ፣ አገልግሎት እና ግብርና ዘርፎች) የሚሆን መሬት ተዘጋጅቷል፡፡ ከተማዋ ብዙ ኢንቨስትመንት አማራጮች አሏት፡፡ ስለዚህ በሦስቱም ዘርፎች የመሬት ሁኔታ የሚያሳስብ አለመሆኑን ያመላከቱት አቶ ፍሬሕይወት እንደሚሉት፣

የኢንቨስትመንት ሥራ ሁሉንም ባለሀብት የሚያካትት ነው፡፡ ባለሀብቱ ደግሞ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ በሶዶ ከተማ መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ ተጋብዘዋል፡፡ በተለይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ወደ ሶዶ ከተማ መጥተው እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በተለይም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሐሳብ አመንጪነት በተደረገው ‹‹ዲያስፖራዎች ሀገር ቤትን ጎብኙ›› በተባለው ግብዣ ሰፊ እንቅስቃሴ ተካሂዷል፡፡ በዚህ መነሻም እኤአ ከ2023 ጀምሮ ሰፊ የሆነ የዲያስፖራ እንቅስቃሴ ተስተናግዷል፡፡ በተለይም ከአምና ጀምሮ የነበረው እንቅስቃሴ ሲስተዋል በቁጥር 30 የሚሆኑ ዲያስፖራዎች በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የከተማውን ውሳኔ ማግኘት በመቻላቸው ወደቀጣዩ ምዕራፍ እንዲሸጋገሩ ተደርገዋል፡፡ በተለያዩ ዘርፎች ኢንቨስት ለማድረግ ባቀረቡት ጥያቄ መሠረትም የከተማ አስተዳደሩን ውሳኔ አግኝተዋል፡፡

# ጎሜ

# ታሪክ ዘካሪ ብቻ ሳንሆን ታሪክ ሠሪም እንሁን

**አሲሴሮ**

እኤአ 1871 ቅኝ ገዢ ሀገራት አፍሪካን ለመቀራመት በርሊን ላይ ስምምነት አደረጉ። በስምምነቱ መሰረትም የወቅቱ ቅኝ ገዢዎች የአፍሪካ ሀገራትን ቀስ በቀስ በመዳፋቸው ስር ማድረግ ጀመሩ፡፡ የአፍሪካ ሀገራትም ስር ለሰደደ ጭቆና፤ ባርነት፤ ጉስቁልናና እንግልት ተዳረጉ፡፡

የቅኝ ገዚዎቹ አንዷ አካል የነበረውም የጣሊያን ወራሪ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመግዛት ተነሳ፡፡ በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ቀስ በቀስ የወረራ አቅሙን እያጠናከረ በኢትዮጵያ ላይ የበላይነቱን ለማሳየት ሞከረ፡፡ ይህንኑ በተግባር ለመሞከርም የውጫሌ የአማርኛና የጣሊያንኛ ትርጉሙ የተለያየ እንዲሆን በማድረግ በአንቀጽ 17 «የኢትዮጵያ መንግሥት ማንኛውንም ግንኙነት ሲያደርግ በጣሊያን በኩል ይሆናል» የሚል ሀረግ በመሸንቀር ኢትዮጵያን በመዳፉ ስር ለማድረግ የሚያስችል አንቀጽ አሰፈረ።

የወቅቱ መሪ አጼ ምኒልክ የጣሊያንን ሴራ በመረዳት አንቀጹ እንዲስተካከል ቢወተውቱም ጣሊያን አሻፈረኝ በማለቱ የካቲት 23 ቀን 1988 ዓድዋ ላይ ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ገጠሙ። ኢትዮጵያውያንም እስከ አፍንጫው ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀውን ወራሪ የጣሊያን ኃይልን በሰዓታት ውስጥ ድባቅ መቱት ፡፡ለመጀመሪያ ጊዜም ጥቁር ሕዝብ በነጭ ገዢዎች ላይ የድል አክሊል ተቀዳጀ፡፡ ጥቁሮች ከተባበሩ ማንኛውንም ኃይል ድል መንሳት እንደሚችሉ ለዓለም አበሰሩ፡፡

የታሪክ ምሁራን ዓድዋን ሲገልጹት “የኢትዮጵያውያን አንድነት መገለጫ፤ የመላው ጥቁር ሕዝቦችና የነፃነት ታጋዮች የድል ታሪክ ነው” ይሉታል። የዓድዋ ድል ከኢትዮጵያ አልፎ መላው አፍሪካውያን ለነፃነታቸው እንዲተጉና አንድነታቸውን እንዲያጠናከሩ መሰረት የሆነ ታላቅ ድል ስለመሆኑም ይናገራሉ። የጥቁር ሕዝቦች የአሸናፊነት ማሳያም ተደርጎም ይወሰዳል-የዓድዋ ድል።

ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን የድል በዓል ሲሆን ለጥቁር ሕዝቦች ደግሞ የነጻነት አርማ ሆኖ ዝንተ አለም ያገለግላል፡፡መላው አፍሪካና የካሪቢያን አካባቢ በቅኝ ገዚዎች መዳፍ ስር ወድቆ የባርነት ህይወት በሚመራበት የጨለማ ወቅት ዓድዋ ብርሃን ሆኖ ጭቁን ሕዝቦችን ለነጻነት ታጋድሎ አነሳስቷል፡፡

በ1871 ከተደረገው የበርሊኑ የቅኝ ግዛት ስምምነት ጀምሮም ጥቁር ሕዝቦች ለከፋ የጉልበት ብዝበዛ፤እንግልትና ኢ ሰብአዊ አካኋን ህይወታቸውን ሲገፉ ኖረዋል፡፡ በሰፋፊ እርሻዎች እግሮቻቸው ታስሮ በመንጋ እንደ እንስሳ ሌት ተቀን እንዲሰሩ ተደርገዋል፡፡ በርካቶችም ከአፍሪካና ከካሪቢያን አካባቢዎች እየተወሰዱ ለምዕራባውያን ስልጣኔ ሻማ ሆነው ነደው አልቀዋል፡፡

የአፍሪካ ሀገራትም የሲኦል ተምሳሌቶች ነበሩ። በቅኝ አገዛዝ ጦስ ምክንያት በርካታ አንጡራ ሀብት ወደ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ በገፍ እንዲጓዝ ከመደረጉም በሻገር አፍሪካውያን በገዛ ሀገራቸው የነጮችን የበላይነት አምነው እጅ እንዲነሱ፤እንዲታዘዙና በአጠቃላይም የቅኝ ገዚዎች ንብረት መሆናቸውን እንዲያምኑ በርካታ ተጽዕኖዎች ይደረጉባቸው ነበር፡፡

ሆኖም የቅኝ ግዛትን ቀንበር መሸከም ያቃታቸው ጥቁር ሕዝቦች ከዓድዋ የአይበገሬነትን መንፈስ በመውሰድ ለነጻነታቸው መታገል ጀምሩ። ብዙዎችም በ1960ዎቹ ነጻነታቸውን አወጁ። በምትኩም ዓድዋ ከነጻነት ባሻገርም የፓን አፍሪካኒዝም መነሻ መሰረትም ሆነ። አፍሪካውያንም ወደ አንድነትና ዕድገት እንዲያመሩ መንገዱን የሚጠርገው የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም እውን ሆነ፡፡

የዓድዋ ድል ከአፍሪካና ከካሪቢያን ሀገሮች ባሻገርም በየቦታው ለጥቁር ሕዝቦች ነጻነት የሚሟገቱ ታዋቂ ሰዎችንም አፍርቷል፡፡ እንደ ማርቲን ሉተር የመሳሰሉ ታዋቂ የነጻነት ታጋዮችም በዓድዋ መንፈስ ለነጻነት ታግለው አሸንፈዋል። ታሪካቸውም ዘወተር ከዓድዋ ጋር ተያይዞ ይወሳል።

**ሆኖም ጫናዎችን መቋቋም በመቻሉ ዛሬ ኢትዮጵያ በስንዴ ዘርፍ ባሳየችው ውጤታማነት በዓለም መድረክ ተሸላሚ ስመሆን በቅታለች**

የዓድዋ ድል በየካቲት የተገኘ የድል እና የነጻነት በዓል በመሆኑም በአሜሪካውያን ዘንድ የየካቲት ወር የጥቁር ሕዝቦች የታሪክ ወር ተብሎ በየዓመቱ ለመዘከር በቅቷል፡፡አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራትም ቀኑን በመዘከር ነጻነታቸውን በማጣጣም ላይ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ህልውና የተረጋገጠበት የድልና የነጻነት በዓል ከመሆኑም ባሻገር በቀጣይ የአፍሪካ ሀገራት ለሚመሰርቱት የኢኮኖሚ ውህደት ጉልበት ሆኖ ያገለግላል። ትናንት ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ለነጻነታቸው እንዲታገሉ እንዳነሳሳ ሁሉ ዛሬም የአፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ነጻነታቸውን እንዲያውጁ ብርታት ይሆናቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሉአላዊነቱ ቀናኢ ነው። በየዘመናቱም ከውስጥና ከውጭ የተቃጡ ሉአላዊነትንና የግዛት አንድነትን የሚፈታተኑ ተግባራትን በጽኑ ታግሎ ሀገሪቱን ከነሙሉ ክብሯ ለአሁኑ ትውልድ አስረክቧል፡፡

ከጥንት እስከ ዛሬ የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶች ከሀገር ውስጥ ባንዳዎች ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ለመበታተን መሄድ እስከሚችሉት ድረስ ተጉዘዋል። ሆኖም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩ ዳር ድንበር የሚዋደቅ፤ ከራሱ በፊት ሀገሩን የሚያስቀድም፤ቀኝ ገዢዎችንና ሌሎች ወራሪ ኃይላትን አሳፍሮ የሚመልስ ጀግና ሕዝብ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ሀገራት ነጻነትና እኩልነት የሚታገሉ፤በአፍሪካ የነጻነት ተምሳሌት የሆኑ ኩሩ ሕዝቦች ናቸው። ይህም ጀግንነትና አይበገሬነት በተባበሩት መንግሥታት ጭምር እውቅና አግኝቶ ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን በሩዋንዳ፤ በቡርንዲ፤በላይቤሪያና በሶማሊያ ተሰማርቶ ጀግንነቱን አስምስክሯል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከዓድዋ እስከ ማይጨው፤ዶጋሊና ሶማሊያ ወረራ ድረስ ህይወታቸውን በመገበር፤ደማቸውን በማፍሰስ እና አጥንታቸውን በመከስከስ በመስዋዕትነት ሀገራቸውን አጽንተዋል፡፡ታሪክም ሰርተዋል፡፡

ይህስ ትውልድ ምን ይመስላል፡፡ለታሪክ እየሰራ ነው ወይስ ታሪክ እየዘከረ መኖር መርጧል። የአባቶቻችን ታሪክ ሁልጊዜም ቢነሳና ቢዘከር እንኳን ለእኛ ለመላው ሕዝብ በሙሉ የሚሰለች አይደለም። ሆኖም ትውልዱ ይህንን ታሪክ ብቻ በማወደስ መጠመድ የለበትም፡፡የራሱን ታሪክ መጻፍ መጀመር አለበት፡፡ታሪክ አውሪ ብቻ ሳይሆን ታሪክ ሰሪም ሊሆን ይገባል፡፡

ሀገር የምትቀጥለው በትናንት ታሪክ ብቻ ሳይሆን በዛሬም ተግባራዊ ሥራ ነው፡፡ ዛሬ ካልተሠራ ነገን ማየት አይቻለም፡፡ወይንም ዛሬ ያላስቀመጡት ነገ ታሪክ አይሆንም፡፡ ትናንት አባቶቻችን የሀገርን ዳር ድንበር ለማስከበር በዱር በገደሉ አጥንታቸውን ከስክሰዋል፤ደማቸውን አፈረሰሰዋል፤ህይወታቸውን ሰጥዋል፡፡ ምናልባት የዛሬው ትውልድ ይህ የሕይወት መስዋዕትነት መክፈል ላያስፈልገው ይቻላል፡፡

የዛሬው ትውልድ መሆን ያለበት የሰላም አርበኛ መሆን ብቻ ነው፡፡ ለሀገር ሉዓላዊነትና ለግዛት አንድነት የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ጀግኖች ውለታ የሚመለሰው የሰላምና የልማት አርበኛ መሆን ስንችል ነው፡፡ በተለይም ሰላም ለራቃት ሀገራችን የሰላም አምባሳደር በመሆን የአባቶቻችንን መስዋዕትነት ከንቱ እንዳይሆን የበኩላችንን ጥረት ልናደርግ ይገባል፡፡

የግጭት፣የጦርነት፣ያለመግባባት ታሪካችን ተዘግቶ በጋራ ታሪኮቻችን ላይ የምንግባባ፤ለጋራ ሀገራችን የምንተጋ፣ ለልጆቻችንም የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማውረስ የጋራ ዕሳቤ የጨበጥን አዲስ ትውልድ መሆን ይገባናል፡፡

ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በምክክርና በመግባባት ነው፡፡ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባትም እንደሀገር የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባ አንድ አመት ከስድስት ወራት አስቆጥሯል፡፡ በእነዚህ ጊዜያትም ምክክሩ የሚመራበትን አቅጣጫ ከመቀየስ ጀምሮ የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮዎችን የመቀመርና በምክክሩ የሚሳተፉ ሰዎችን የመለየት ስራዎች ተከናውነዋል።በቀጣይም የምክክሩን አጀንዳዎችን ከህብረተሰቡ የመቀበልና ምክክሩን ወደ መሬት የማውረድ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

ስለሆነም ሀገራዊ ምክክሩ የቀድሞ ችግሮቻችን፤ አሁን ያሉት ችግሮቻችን መፍቻና በቀጣይም ተመሳሳይ ችግሮች እንዳያጋጥሙን የመፍትሄ አቅጣጫን የሚጠቁመን መድህን መሆኑን ማመን ይጠበቅብናል፡፡ በሀገሪቱም መተማመን የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመመስረትም እርሾ ሆኖ እንደሚያግዝ እምነት መጣል አለብን፡፡

በቅድሚያ ሁሉም ነገር በንግግር እና በምክክር ይፈታል የሚል እምነት ማዳበር ይጠበቅብናል፡፡ ወሰንም ሆነ የማንነት ጥያቄ እንዲሁም ራስን በራስ ማስተዳደር እና የፍትህ ጥያቄዎች በአጠቃላይ የፖለቲካ ጥያቄዎች እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በሙሉ በሀገራዊ ምክክር ሊፈቱ የማይችሉበት ምክንያት አይኖርም፡፡

አሁን ያሉት አለመግባባቶች ተወግደው በፍቃደኝነት እና በመግባባት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ምክክሩ የማይተካ ሚና አለው፡፡ሀገራዊ ምክክሩ ከዘመን ወደ ዘመን ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን ለመፍታትና የመወያየትና የመነጋገር ባህልንም ለማዳበር ይረዳል። በመወቃቀስ ላይ የሚያተኩረውንም የፖለቲካ ባህላችንንም ወደ መነጋገር፤መተባበርና መደጋገፍ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡

ስለዚህም ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል፡፡ ከመነጋገር ይልቅ በር ዘግቶ መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል፡፡ አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፤ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው።

ስለዚህም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል፡፡ የስልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነውና፡፡ በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ የሀገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው፡፡ ጽንፍ ለጽንፍ ሆኖ ቃላት መወራወርና ይዋጣላን ማለት እንደሀገር ዋጋ አስከፍሎናል፡፡ በዚህም መንገድ ለዘመናት ተጉዘን ያተረፍነው ድህነትን፤ኋላቀርነትና ዕልቂትን ብቻ ነው።

ስለሆነም የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን በአባቶቻችንና እናቶቻችን ተጋድሎ ያገኘነው ኩራትና ነጻነታችን ሙሉ እንዲሆን ሀገሪቱን በልማት ማበልጸግ ያስፈልጋል። ይህ ትውልድ ታላቁን የዓባይ ግድብ ሰርቶ እያገባደደ ነው፡፡ ይህን የሀገር ኩራት የሆነ ግድብ አጠናቆ ለሀገር ብሎም ለአፍሪካ ብርሃን ማጎናጸፍ የዚህ ትውልድ አንዱ አደራ ነው፡፡

በግብርና ልማት በተለይም በስንዴ የተገኘውን አኩሪ እንቅስቃሴ ዘላቂ ማድረግና ከኢትዮጵያም አልፎ አፍሪካን መመገብ ሌላው የዚህ ትውልድ አሻራ ሊሆን ይገባል፡፡ በርካታ የውጭ ኃይላት ኢትዮጵያ ስንዴ ማምረቷ ከተጽዕኖና ከተንበርካኪነት እንድትወጣና ሌሎች የአፍሪካ ሀገራትም ፈለጓን ይከተላሉ በሚል ስጋት ኢትዮጵያ ላይ የተለያዩ ጫናዎችን ሲፈጥሩ ቆይተዋል፡፡ሆኖም ጫናዎችን መቋቋም በመቻሉ ዛሬ ኢትዮጵያ በስንዴ ዘርፍ ባሳየችው ውጤታማነት በዓለም መድረክ ተሸላሚ ለመሆን በቅታለች፡፡

አረንጓዴ አሻራ በማኖር ረገድ ኢትዮጵያውን ባለፉት አምስት ዓመታት አዲስ ታሪክ በመጻፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ አኩሪ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን ልማትና ዕድገት የማይወዱ አካላት ሊያጣጥሉት ቢሞክሩም ተግባሩ የሚደበቅ አይደለምና ኢትዮጵያ በተሳተፈችባቸው መድረኮች ሁሉ በውጤታማነቱ እየተወሳ ይገኛል፡፡ ስለዚህም ትውልዱ ይህንን አንፀባራቂ እንቅስቃሴ ከዳር ማድረስና ኢትዮጵያን ብሎም አፍሪካን አረንጓዴ ማልበስ ቀጣይ የቤት ስራው ሊሆን ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል የሀገርን ዳር ድንበር አላስደፍርም በማለት ደማቸውን በማፍሰስ፤አጥንታቸውን በመከስከስ ውድ ህይወታቸውን መስዋዕት ሲያደርጉ ኖረዋል። የአሁኑ ትውልድም የሀገሩን ዳርድንበርና ሉአላዊነት ከመጠበቅ ጎን ለጎን በሰላም እና በልማቱም መስክ ሀገሪቱን ወደ ፊት ሊያራምዱ የሚያስችሉ ተግባራትን በመፈጸም መስዋዕት የከፈሉ ቀደምት አባቶቻችንን ፈለግ ሊከተል ይገባል፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## በፈረጃ ዱካ!

ሙሉጌታ ብርሃኑ



በሕዝብ ገንዘብ በሚሠራው የመጀመሪያ ፊልም ከ4 ሺህ ሰው በላይ እንደሚሳተፍ አዘጋጆቹ ገልጸዋል፤

ስለ ኢትዮጵያ ፊልም ሲነሳ ብዙዎች ያላቸው አመለካከት ትዝብት ውስጥ የሚወድቅ ነው፡፡ አንዳንዱማ የኢትዮጵያ ፊልም ጉዳይ ሲነሳ አውሊያው እንደተነሳበት ጠንቋይ ሊርገፈገፍ ሁሉ ይችላል፡፡ የባህር ማዶውን እንጂ የኢትዮጵያን ፊልም አለማየት እንደስልጣኔ የሚቆጥሩም በሽ ናቸው፡፡

ትልቁ ችግር በፊልሞቹ መንገሸገሻችን ሳይሆን እኔስ የበኩሌን ምን አደረግሁ? ብለን አለመጠየቃችን ነው፡፡ ትችት ያለ ነገር ቢሆንም ከራስ ሲጀምር መልካም ነው፡፡ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተን ለትችት የሚያበቃ ሥራ አልሰራንም፡፡ አሜሪካውያን ለገናናው የፊልም ኢንዱስትሪያቸው ዛሬም ድረስ በኩራት የሚያወሩትን አንድ ነገር ሠርተዋል፡፡ በፊልሙ ጥበብ የበለጸጉ ሆነውም ሁሌም በምሳሌነት እናነሳቸዋለን፡፡ በእርግጥ አፍሪካውያንም እንደ ናይጄሪያ አይነቶቹን አንረሳም፡፡

ሆሊውደ የተመሰረተው በራሱ አቅም እንዳይመስላችሁ፤ በሕዝብ ገንዘብ ነው፡፡ ሆሊውድም የአንድ ትልቅ ባለሀብት ወይንም የራሱ ብቻ አይደለም። ሆሊውድ መላው አሜሪካውያን እንደ ዓይን ብሌናቸው የሚመለከቱት የራሳቸው ንብረት ነው፡፡

የአሜሪካ የፊልም ጥበበኞች ልክ እንደዛሬ እንደኛው የፊልም ኢንዱስትሪ ባለቤት ከመሆናቸው በፊት ፊልም የሚሠሩት ፕሮዲዩስ የሚያደርጋቸውን ባለሀብት እየፈለጉና እየተለማመጡ ነበር፡፡ ከዚያም ኋላ ባለገንዘቦቹ ባለቤት ናቸውና እንዳሻቸው ይዘውሯቸው ነበር፡፡ ስለፊልሙ ምንነት ያልገባቸውም ናቸውና ባለሙያዎቹን የሚያስጨንቁት ትርፍ እንዲያመጡላቸው ብቻ ነው፡፡

ሌላው ነገር ግድ አይሰጣቸውም፡፡ በዚህም ላይ ትርፉን ለራሳቸው ብቻ በማግበስበስ፤ ለፊልሙ የሚደክሙት አንድም ጠብ የሚል ርስት ለማግኘት አልቻሉም፡፡ በዚህ ሁሉ ምርር ስልችት ያላቸው የፊልሙ ጠቢባን ተሰባስበው ተማከሩ፤ አወጡ አወረዱ፡፡ ድንገት ግን አንዲት ሀሳብ ብልጭ አለችላቸው፡፡ ይህም የሕዝብ ፊልም መሥራት የሚል ነበር፡፡ እናም ሕዝባቸውን በማስተባበር ገንዘብ ሰበሰቡ፡፡ እንደቀድሞው ፕሮዲዩስ የሚያደርጋቸው አካል እግር ላይ መውደቁ ቀርቶ በሰበሰቡት ገንዘብ ፊልም ሠሩ፡፡

በአንድ አልቆሙም፤ ሁለት...ሦስት... እያለ ቀጠለ። በዚህም የቀድሞ ባለሀብቶችንና ፕሮዲዩሰሮችን ከጨዋታ ውጪ አደረጓቸው፡፡ ነገሩ እያማረበትና ተመልካችም የሚፈልገውን እያገኘ፤ ቁጥሩም እየጨመረ ሄደ፡፡ የገንዘብ አቅማቸውም ፈርጣማ ሆነና በአጭር ጊዜ ውስጥ የሆሊውድ የፊልም መንደርን አቋቋሙ፡፡ በመሳሪያና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እራሳቸውን በሚገባ በማጠናከር ከሀገራቸው አልፈው መላው ዓለምን ያጥለቀልቁት ጀመር፡፡

በአንድ ፊልም የተጀመረችው ትንሽ ሀሳብ ዛሬ የስኬት ጫፍ ላይ ደርሳለች፡፡ የፊልም ጥበብ በቁሙ ሳር የሚበቅለበት መቼ መሰላችሁ?፤ የንግድና የሸቀጥ የሆነ እለት ነው፡፡ የዚያኔ ጥያቄው ምን በምን መልኩ ሰርቼ የፊልሙን ኢንዱስትሪ ላሳድገው ሳይሆን ምኑን ከምኑ አድርጌ ኪሴን ልሙላው ይሆናል፡፡ ስለዚህ ዓላማውም ማስደሰት የሚፈልገውን አካል አስደስቶ የማይሞላውን ሆድና ኪስ መሙላት ነው፡፡ ፕሮዲዩስ የሚያደርጉ አካላት ስለ ፊልም ካልገባቸው ዘርፉ የንግድ ብቻ መሆኑ አይቀርም፡፡ ስለዚህም ዋናው ነገር `የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው` ነው፡፡

ባለሀብቶች ፕሮዲዩስ ማድረጋቸው ባልከፋ፤ ግን ደግሞ ሌላ ያስከተለው ጦስም አለ፡፡ የፊልም ኢንዱስትሪው እራሱን ችሎ እንዳይቆም አድርጎታል። እንዴት? ሲባል ከፊልሞቹ የሚገኘው ትርፍ በሙሉ ተጠራርጎ የሚገባው ወደ ኢንዱስትሪው ሳይሆን ወደ ባለሀብቶቹ ፕሮዲዩሰሮች ኪስ ነው፡፡ ተረቱም፤ `ላለው ይጨመርለታል` ነውና ከተዋንያን እስከ ትልልቅ ባለሙያዎች የሚያዋጣው የፊልሙ ኢንዱስትሪ የሚያገኘው የሻይ መጠጫ ነው፡፡

የሀገራችን የፈረጃ ፊልም ሀሳብ ታዲያ በሻይ መቃጠሉ በዚህ ይብቃና ሁላችንም ችለን እናስችል የሚል ሆኖ ብቅ ብሏል፡፡ ጽንሰ ሀሳቡ ከላይ ካነሳነው ከሆሊውድ የፊልም ኢንዱስትሪ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ልክ እኛ ሀገር ውስጥ እንደምንመለከተው ሁሉ በኛ የፊልም ኢንዱስትሪ የነበሩ ችግሮች በሙሉ እነርሱም ዘንድ ነበሩ፡፡

በፖለቲካም ይሁን በኪነ ጥበብ ነጻነት ማለት ሕዝብ ነው፡፡ ከነበርንበት እቅፍ አምልጠን በሕዝብ እቅፍ ውስጥ ስንገባ የዛኔ ነው ነጻና የሕዝብ አገልጋይ የምንሆነው፡፡ ታዲያ የፊልሙን ኢንዱስትሪ ከነጋዴው አስጥለን እኛም የምንፈልገው አይነት ፊልም ማየት እንድንችል ነጻነት አያስፈልገውም?፡፡ በእርግጥ የፊልም አፍቃሪና ወዳጆች ብቻም ሳይሆኑ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለፊልሙ ይህ ነጻነት አያስፈልገውም የሚል እምነት አለው ተብሎ አይታሰብም፡፡

“ፈረጃ” በሕዝብ ሊሠራ የተዘጋጀ የሕዝብ ፊልም ነው፡፡ በዚህ ታላቅ ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ፤ “ፈረጃ” ማን ነው? ማንስ እንበለው?፣ ፈረጃ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የበኩር ፊልሙ ነው፡፡ ምክንያቱም እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ገንዘብ የሠራው ፊልም ባለመኖሩና በፈረጃ ደግሞ በመጀመሩ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜም በፊልማችን ውስጥ የሚጠቀሰው የፕሮዲዩሰር ስም ከባለሀብቶችና ተቋማት ውጪ ሊሆን ነው፡፡

ከሦስት ዓምታት በፊት የዚህ ፊልም ሀሳብ ተወለደ። በማን? በትወና ብቃቱ ብዙኃኑን ሲያስደምም በቆየው በወጣቱ ተዋናይ ሔኖክ ወንድሙ ነው። ሔኖክ ይህን ለመሥራት እንዴትስ አሰበ? ከቀናቶች በፊት ፊልሙ የደረሰበትን ደረጃ ለሕዝብ ለማሳወቅ ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ እንዲህ ሲል አብራርቷል፤ “እኔ አንድ ኢትዮጵያዊ ነኝ። ዛሬ እዚህ ጋር በክብር እንድቆም ያደረገኝ የኢትዮጵያ ፊልም ነው። ታዲያ እኔን ያስከበረኝ ፊልም፤ ዛሬ ላይ ሲበላሽ እንዴትስ ዝም ብዬ አያለሁ...ምን የመቀየር ምኞት ቢኖረኝ ለብቻዬ ልለውጠው የምችለው አልነበረም። እናም አሰብኩ። በተለያዩ ሀገራት ስዘዋወር የተመለከትኩትን ተሞክሮ ለሀገሬ ፊልምም ቢሆን ብዬም ተመኘሁ። እናም፤ የኢትዮጵያን ፊልም ሊለውጥ የሚችለው እራሱ ሕዝቡ እንደሆነ ተረዳሁ። እኔም ማድረግ የምችለው ይህን ነበር፤ ፊልሙን ለሕዝብ መስጠት። ከዚህ በመነሳትም ለማሳያ የሚሆን አንድ ነገር ማድረግ ነበረብኝ፤ ከልጅነቴ ጀምሮ የማውቀውን “ፈረጃ” የተሰኘ ግለሰብን ታሪክ፤ ለዚህ አጨሁት፡፡ እናም ይህን ታሪክ ወደ ፊልምነት በመቀየር ሁሉንም ነገር ማድረግ እንደምንችል ለማሳየት፤ ሀሳቤን ይዤ ወደ ሕዝቡ ዘንድ ሄድኩ፤ ሕዝቡም አላሳፈረኝም። እኔ “ፈረጃ” ስል ጀምሬዋለሁ፤ ነገ ላይ ደግሞ ይህን የተመለከተ ሌላውም ይቀጥላል”፡፡

ለኛ የፊልም ኢንዱስትሪ የሚያስፈልገው ይሄው ነው፡፡ ፊልማችን ተለውጦ ለማየት ሌላ ተአምር አያስፈልገንም፡፡ “አንድነት ኃይል ነው...ድር ቢያብር አንበሳ ያስር...ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፤ ለሃምሳ ሰው ጌጡ...” እያልን ስንፎክርና ስንተርት የምንኖር እኛን ቀርቶ በሕዝብ ፊልም ሆሊውዶች እንኳን የደረሱበትን አይተናል፡፡

ፈረጃ ከየት ተነስቶ የት ደረሰ? የፊልሙ ግራና ቀኝ አዝማቾች ለዚህ ጥያቄ፤ ለሚጠብቃቸው ሕዝብ በመግለጫው አስረድተዋል፡፡ የፊልሙ ደራሲና አስተናባሪ ሔኖክ ወንድሙ፤ የሮዝ ፊልም ኢንተርቴመንት ባለቤት ግሩም ብርሀነ ጻሐይ እና የኢነርጂ ፊልም ፕሮዳክሽን ሥራ አስኪያጅ ዳንኤል ግርማ፤ በኢትዮጵያ የፊልም ኢንዱስትሪ ውስጥ የመጀመሪያውን ታሪክ ለመሥራት ጥምረት ፈጥረዋል። በጋራ ለመሥራት የመጀመሪያቸው አይደለም፤ ከዚህ ቀደም በፊልም ያቤጽ፣ ምናለሽ፣ ቁራኛው፣ ሀገር ስጪኝ እንዲሁም ከሙዚቃ ሥራዎች ደግሞ የቴዲ አፍሮን ማር እስከ ጧፍ ቪዲዮን ጨምሮ በበርካታ ሥራዎች ውስጥ ተቀናጅተው ሠርተዋል፡፡ አሁን ደግሞ ይሄው በ”ፈረጃ” ፊልም፤ እንችላለን ብለው ተነስተው ከሕዝብ አደራን ተቀብለዋል፡፡ ሕዝቡም ከኪሱ ገንዘብ አውጥቶ ሲሰጥ እነርሱን አምኖና የሀገሬን የፊልም ኢንዱስትሪ ይለውጣል በማለት ተስፋ ነው፡፡

እንዳደግንበት ባህላችን አደራን የተሸከመ እንቅልፍ የለውምና የፊልሙ አዘጋጆች፤ ፈረጃ በአሁኑ ሰዓት ሁሉን አጠናቆ ወደ ቀረጻ ለመግባት በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ፊልሙን ለመሥራት የተመደበለት የገንዘብ መጠን 3.7 ሚሊዮን ብር ሲሆን፤ እስከዛሬ ድረስ በጎ ፈንድ ሚ፤ ከሕዝብ ለመሰብሰብ የተቻለው የገንዘብ መጠን 2.6 ሚሊዮን ብር ነው፡፡ ታዲያ ይህ ፊልሙን ያሠራል?፤ ለዚህ ጥያቄ መልስ የሰጠው ሔኖክ ወንድሙ እንዲህ ብሏል “የተሰበሰበው ብቻ ፊልሙን ያሰራል ወይ፤ አያሰራም፡፡ ግን ሕዝባችን ደግነቱን አሳይቶኛል፡፡ ያውም በዚህ የችግር ሰዓቱ ካለችው ላይ አንስቶ ሰጥቶናል፤ በእጅጉ ምስጋና ይገባዋል፡፡ ከአሁን ወዲያ፤ ሕዝቡን ለማስጨነቅ እኔ በግሌ አልፈልግም። ከራሳችን ኪስ አውጥተንም ቢሆን የቀረችዋን እንሞላታለን፡፡ የፊልሙ ቀረጻም በቅርቡ ይጀምራል”።

አዘጋጆቹ ይህንን ፊልም ከሕዝብ ተቀብሎ መልሶ ለሕዝብ መስጠት በሚል ዓላማ ተነስተዋል። ግን ታዲያ ሕዝቡ በምን መልኩና እንዴትስ ነው ሊሳተፍበት የሚችለው? ለሚለው ጥያቄ፤ እንቅስቃሴው “አምስት ብር ከፍሎ ፊልም መመልከት” የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት ይመለከተኛል የሚል አንድ ሰው ለዚህ ፊልም የ5 ብር የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ድር ቢያብር.. ማለት እንግዲህ እዚህ ጋር ነው፡፡

ለፊልሙ ወጪ ያስፈልጋል የተባለው 3.7 ሚሊዮን ብር ነው፤ ይህን በሂሳባዊ ቀመር ብናሰላው፤ ከ90 ሚሊዮን በላይ ከሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል 7 መቶ አርባ ሺህ ሰው፤ እያንዳንዱ አምስት አምስት ብር ብቻ ቢያዋጣ ፊልሙን ሠሩት ማለት ነው፡፡ መላውን ሕዝብ ትተን፤ የፊልም አፍቃሪያንና ወዳጆችን ብቻ ብናስብ እንኳን በአንድ ጀንበር ሁለትና ሦስት ፊልሞችን ለመሥራት ይቻላል፡፡ እዚህ ጋርም “ድር ቢያብር፤ አንበሳ ያስር” ልንል እንችላለን፡፡ ታዲያ ይህንን አንበሳ ለማሰር የማይፈልግ ማን ነው?

ገንዘብ ከሕዝብ ተዋጣ፤ ፊልሙም ተሠራ፤ ቀጣይስ? ከፊልሙ የሚገኘው ገቢ ጉዳይ በማን ኪስ ይግባ? በማንም ኪስ አይገባም! የቄሳርን ለቄሳር...ስለዚህ፤ በረሀብ ጥም ለተጎሳቆለው የፊልም ኢንዱስትሪ ይውላል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ከፈረጃ ቀጥሎ የሚወለዱ ሌሎች ፊልሞች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ አዎን ይኖራሉ፤ በፈረጃ ብቻ እንደማይቆም አዘጋጆቹ ተናግረዋል፡፡

በሆሊውድ የፊልም መንደር የጉዞ መነሻና ዛሬ የደረሰበትን ለተመለከተና በቅጡ ለተረዳ፤ እኛም በፈረጃ ፊልም ጅማሮ ላይ እያከልንበት ነገ ላይ ልክ እንዲሁ ለመሆን እንደሚችል አያጠራጥርም። ነገር ግን አንድ ፈረጃ ብቻውን ተውልዶ እሱም ሌላ ሳይወልድ ከመከነ ይሄኔ ጥበብም አልኖረች ፊልምም አልተሰራች፡፡

ታዲያ ፈረጃ ፊልም ይዞ የመጣው አዲስ ነገር ምንድነው? የመጀመሪያው ነገር የዚህ ፊልም ፕሮዲዩሰር ከዚህ ቀደም እንደምንሰማው እገሌ፤ እገሊት የሚባል ነገር የለውም፡፡ አንድና አንድ “የፊልም አድናቂና ወዳጆች” ናቸው። ነገሩ ሲፈታ ሕዝብ እንደማለት ነው። በመቀጠል ለዚህ ፊልም ወጪ የሚደረገው 3.7 ሚሊዮን ብር መሆኑ ነው፡ ፡ ሌላ ወሰን መስበሩ ነው። ይህ ለፊልም ጥራት ማረጋገጫ ባይሆንም ግን ሳይወድ በግዱ ልዩ ማድረጉ አይቀርም። ቀጥሎም በድምሩ የሚሳተፉ ተዋንያንን ቁጥር ስንሰማ ለታላቁ ሩጫ ይመስለን ይሆናል፤ ግን አይደለም። ለታላቁ ፊልም እንጂ፡፡ በትንሹ ከ4ሺህ ሰው በላይ ይሳተፍበታል።

የፊልሙ ዋና ገጸ ባህሪ አንደኛው የሕይወት ክፍል ነው። ቀጥሎም በፊልም ጥበብ ሙያ ለየት ብሎ ከመጣባቸው ነገሮች አንደኛው በቀረጻው፤ የምስልና ድምጽ ጥራቱን ፈርጣማ ለማድረግ የሚጠቀመው መሳሪያ ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁና በአይነታቸው ለየት ያሉ መሆናቸው ነው።

በሌላ በኩል የተመራረጡ የባለሙያዎች ጥምረት ተፈጥሯል። ሌላውና ዋነኛው ነገር ኢንዱስትሪው ለመጀመሪያ ጊዜ ከየትኛውም አካል ጫና ነጻ በመሆን ለራሱ ገቢ ማስገባቱ ነው፡ ፡ ትልቁ ችግር የነበረው የባለሙያዎች፤ የላብ የወዝ ነገር መፍትሄ ያገኛል። በሠሩትና በለፉት መጠን የሚገባቸውን ያገኛሉ፡፡ ከሁሉም ላቅ ያለ ሌላም ትልቅ ጉዳይ አለ፤ ይሄውም የዘርፉና የሙያው ነገር ነው፡፡ እንዲህ ነጻ ካወጣነው፤ ባለሙያውን ይህን ሥራ! ይህን አትሥራ!፤ ያን ቁረጥ! ያን ፍለጥ! የሚል አይኖርም። ስለሆነም የፊልም ባለሙያዎቹ የሚጨናነቁት ትርፍ አግኝቶ ፕሮዲዩሰሩን ስለማስደሰትና ከዕዳ ነጻ ስለማውጣት አይደለም። ጭንቀታቸው ቆንጆ ፊልም ሠርቶ የሚሠሩለትን ሕዝብ ስለማስደሰት ነው፡፡

ሕዝቡም ማየት የሚፈልገውን ነገር ከማየቱም በላይ፤ የኢንዱስትሪው ገቢ መልሶ እራሱኑ የሚደጉም ይሆናል፡፡ በፈረጃ ፊልም የሚገኘው የዋናው ገጸ ባህሪን፤ አንደኛውን የሕይወት ክፍሉን ተከትሎ ከ4 ሺህ እስከ 5 ሺህ ድረስ ያሉ አጃቢ ተዋንያን ይሳተፉበታል፡፡ ይህ ቦታም ፊልም የመሥራት ፍላጎት ላለው ሁሉ ክፍት ስለመሆኑ አዘጋጆቹ ይናገራሉ፡፡

እንግዲህ፤ የሀገሬ ልጅ፤ አይሆንም አትበል፤ ይሆናል፡፡ ፊልም ለቅንጦት ነው አትበል፤ አይደለም። ሌላው ያድርገው አትበል፤ ይህች ሀገር ያላንተ ማንም የላትምና፡፡ አንድ ቀን አደርገዋለሁም አትበል፤ ዛሬም ያው አንድ ቀን ነውና፡፡ ይህን ስል ስለ ፈረጃ ፊልም ብቻም አይደለም፡፡ እነርሱ ጀምረውታል ሌሎች ለቀጣዩ ይዘጋጁ፡፡ ከአጋም ጋር ለተጣበቀ ቁልቋል ከዚህ የተሻለ ምንም መፍትሄ የለውም፡፡ በፈረጃ ዱካ ስንል፤ ዱካ አንድም ያስቀምጣል፤ አንድም ፈለግ ነውና ያስከትላል፡፡

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ትኩረት የሚሻው የሴት ተማሪዎች ንጽህና መጠበቂያ ጉዳይ

**እዮሩስ ተስፋዬ**

ማህሌት መኮንን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ናት፡፡ ማህሌት በአንዲት ሴት ላይ የደረሰን አንድ ታሪክ ልታጫውተን ፈቀደች፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡- አንዲት ዕድሜዋ ከ14 ዓመት የማይዘል የቤት ሠራተኛ ታዳጊ በምትሠራበት ቤት ውስጥ ቡና እያፈላች ነበር፡፡ ይህች ታዳጊ ከተቀመጠችበት ስትነሳ ልብሷ እና የተቀመጠችበት ወንበር የወር አበባ ደም ነክቶታል፡፡ በቤቱ ውስጥ ከማህሌትና ከታዳጊዋ የቤት ሠራተኛ ውጪ ያሉት ወንዶች ብቻ ነበሩ፡፡ ወንዶቹ ይህን ሲመለከቱ ታዳጊዋን ‹‹አይዞሽ›› ከማለት ይልቅ ተጠየፏት፡፡ ይህን ያስተዋለችው ማህሌት ግን ሞዴስ ገዝታ አጠቃቀሙን ለታዳጊዋ አስረድታ እንዳትረበሽ ብትነግራትም፤ ታዳጊዋ ለረዥም ሰዓት በድንጋጤ እና በሃፍረት ውስጥ ነበረች። ማህሌት ከዚህ የተገነዘበችው ታዳጊዋ ባደገችበት አካባቢ ስለወር አበባ ጉዳይ ማንሳት እንደ ነውር እንደሚቆጠር ነው።

ማህሌት አብረዋት በሚማሩ ሴቶች ላይ ሳይቀር የወር አበባ መደናገጥና ፍርሀት ሲፈጥር እንደታዘበች ትናገራለች። ከዚያም አልፎ ገና ለገና ደም ይነካብኛል፣ ሞዴስ ቶሎ ቶሎ እንዳልቀይር ደግሞ ያልቅብኛል የሚል ስጋት አድሮባቸው እንቅስቃሴያቸው የተገደበ መሆኑንም ተረድታለች፡፡ ያምሆኖ በአንፃራዊነት በከተሞች አካባቢ ያለው አመለካከት የተሻለ እንደሆነ ትናገራለች፡፡ ይሁን እንጂ ይህን የግንዛቤ ክፍተት ለመቅረፍ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልፃለች።

የወር አበባ ሲመጣ ሴቶች ከሚያስተናግዱት ህመም በተጨማሪ ‹‹ለሞዴስ መግዣ ብር ከማን ልጠይቅ?›› ብለው የሚጨነቁ ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ችግር በከተሞች አካባቢ አለን ብሎ ለማሰብ የሚከብደው አይጠፋም፡፡ ችግሩ በስፋት እንዳለም የተረዳው ብዙ አይደለም፡፡ ሴቶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከትምህርት ቤት ይቀራሉ፡፡ መቅረታቸው ስለሚያማቸው ብቻ አይደለም። የንጽህና መጠበቂያ እንደልብ ስለማያገኙ ልብሳቸው ደም እንዳይነካ በመፍራት እንጂ፡፡

የሥነልቦና ተማሪዋ ማህሌት በዚህ ጉዳይ ላይ ቁጭቷን ስትገልፅ፣ ‹‹በጤና ተቋም ውስጥ ኮንዶም በነፃ ይሰጣል፡፡ ነገር ግን ሞዴስ (ፓድ) በየሱቁ ይሸጣል፤ ይህ በፍፁም ትክክል አይደለም፡፡ ጉዳዩ በደንብ ሊጤን ይገባል፡፡ የወር አበባ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ያለጊዜው ማስቆም አይቻልም ስለዚህ በነፃ መታደል አለበት›› በማለት ትናገራለች፡፡

ወይዘሮ ሀናን አህመድ የሀንስ ዊዝ ኬር መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ ናት፡፡ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በነበረችበት ወቅት የደረሰባትን ነገር በማስታወስ መሰል ታሪኳን አጋርታለች። ወይዘሮ ሀናን በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ እያለች ልብሷ በወር አበባ ደም ተበላሸ፡፡ ሹራቧን ወገቧ ላይ አሥራ ሌሎች እንዳያዩባት ሸፈነችው፡፡ ወደ ቤቷ መሄድን ናፈቀች፡፡ ተሸማቀቀች፡፡ በሀፍረት የሌሎችን ዓይን ላለማየት ‹‹አሞኛል›› በሚል ሰበብ ለሳምንት ከትምህርት ገበታዋ ትቀራለች። በቂ ግንዛቤ ስላልነበራት ብዙ ከባድ ጊዜዎች አሳልፋለች። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለችም ቢሆን አንድ ፓድ ለምን ያህል ጊዜ መጠቀም እንደሚቻል ግንዛቤው ስላልነበራት ለኢንፌክሽን ተጋለጠለች፡፡ እነዚህ ነገሮች ተደማምረው ወደ ትዳር ዓለም ስትገባ ተደጋጋሚ ውርጃ አጋጠማት። በሀኪሞች መውለድ እንደማትችል ተነግሯታል። እርሷ የደረሰባት ችግር እርሷ ላይ ብቻ እንዲቀር ዛሬ ላይ ታሪኳን በማጋራት ግንዛቤ በመስጠት እየሠራች ነው። ደግሞም ታጥቦ ዳግም ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የንጽህና መጠበቂያ ምርቶችን እያመረተች ትገኛለች፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት ሀንስ ዊዝ ኬር ከዳሸን ባንክ ጋር በመሆን ‹‹ማንኛዋም ሴት በንጽህና መጠበቂያ ምርት እጥረት ከትምህርት ገበታዋ መቅረት የለባትም›› በሚል ሃሳብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መልሶ መጠቀም የሚቻል እንዲሁም ከ12 ወራት እስከ 18 ወራት ድረስ የሚያገለግል የንጽህና መጠበቂያ ምርቶችን በዩኒቨርሲቲ ለሚማሩ አንድ መቶ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁለት ሺ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡



**አንድ መቶ አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁለት ሺ ሴት ተማሪዎች የንፅህና መጠበቂያ ድጋፍ ተደርጓል፣**

እንደ ወይዘሮ ሀናን ማብራሪያ፣ ‹‹የታብብ የንጽህና መጠበቂያ እንቅስቃሴ›› ከተማው ላይ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያሉ ተማሪዎችን ለመርዳት ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲው የሚማሩ አብዛኞቹ ተማሪዎች ከክፍለ ሀገር የመጡ ናቸው፡፡ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢ ባለው የሰላም መደፍረስ ቤተሰብ ገንዘብ ለመላክ ይቸገራል። ቢያንስ የፓድ ሃሳባቸውን ለማቅለል ድጋፍ ማድረግ አስፈልጓል። በተጨማሪም ጭንቀታቸውን በማቃለል ትምህርታቸው ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ የሚግዝ ነው፡፡

የንጽህና መጠበቂያ እጦት በከተማ ደረጃ አለ ብሎ ማሰብ ከባድ ቢመስልም ችግሩን ለማወቅ ወደ ትምህርት ቤቶች ሄዶ መጠየቅ ብቻ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ መረዳት ይቻላል የምትለው ወይዘሮ ሀናን፤ ነገር ግን ችግሩ ብዙ አልተነገረም ብላ ታምናለች፡፡ ጉዳዩ አሳፋሪ እንዳልሆነ እና ተፈጥሯዊ እንደሆነ ለማስረዳት ብዙ መሠራት አለበትም ትላለች፡፡ በቀጣይም የሴቶችን ቀን ምክንያት በማድረግ ታራሚ ቤት ላሉ ሴቶች ድጋፍ ለማድረግ ተሰናድታለች፡፡ ከዚህ ባሻገር ወደ ትምህርት ቤቶች፣ ተፈናቃዮች፣ የሃይማኖት ተቋማት (ሴት ገዳማውያን) በማቅናት ድጋፍ ለማድረግ እና ለመድረስ እንደምታሠራ ቃል ገብታለች፡፡

እንደ ጀማሪ ድርጅት እስከዛሬ ለ10 ሺ ሴቶች ድጋፍ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፤ ድርጅቱ ከሚያገኘው ትርፍ አንድ በመቶ በጎዳና ላይ ለሚገኙ ሴቶች የሚያደርስ መሆኑን የጠቆመችው ወይዘሮ ሀናን፣ መንግሥት ከንጽህና መጠበቂያ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ተመልክቶ ቢሠራበት መልካም ነው የሚል ሃሳብ አላት፡፡ አንዲት ሴት ትምህርት ቤት ስትገባ የትምህርት ቁሳቁሶች እንደሚያስፈልጓት ሁሉ የንጽህና መጠበቂም ያስፈልጋታል፡፡ ዋናው ቁምነገሩ ሴቷ እንድትበቃ ማድረግ ነውና ድጋፍ ማድረግ ቢቻል ብዙ ሴቶች ጋር መድረስ ይቻላል በማለትም ሃሳቧን አካፍላለች።

ዶክተር ሰውዓለም ፀጋ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነልቦና የትምህርት ክፍል መምህርት ናቸው። በተጨማሪም በዩኒቨርሲቲው የሥርዓተ ጾታ እና ኤችአይቪ መከላከል ዳይሬክተርም ናቸው፡፡ የወር አበባ ጉዳዩ በቀጥታ ሴቶችን የሚመለከት ቢሆንም ወንዶችንም ያገባቸዋል የሚሉት ዶክተር ሰውዓለም፣ ‹‹የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ የብዙ ነገር እጦት አለበት፣ ለጥናት ሲባል የእንቅልፍ እጦት አለበት፡፡ የገንዘብ እንዲሁም ከሰዎች የመገናኘት (የሶሻል ወርክ ኔትዎርክ) እጦት አለበት ብለን ብንናገር ማጋነን አይደለም፤ የንህጽና መጠበቂያ ቁሳቁስ እጦት ደግሞ ሴት ተማሪዎችን የሚፈትን ነገር ነው›› ይላሉ። በአሁኑ ወቅት ዋጋው እየተወደደ መሆኑን በመግለፅም ተማሪዎችም ለመግዛት ሲቸገሩ እንደሚመለከቱ ይናገራሉ። ስለዚህም መልሶ መጠቀም የሚቻል የንፅህና መጠበቂያ ለሴት ተማሪዎች መሰጠቱን አመስግነዋል፡፡

በዳሸን ባንክ ሴት ሰፖርቲንግ አክተር ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ወይዘሮ እስከዳር አሊ ስለ ድጋፉ ሲናገሩ፤ ባንኩ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የተለያዩ ተግባራትን እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ ቀደም ከሀንስ ዊዝ ኬር ጋር በመተባበር ለአንድ ሺ ሴት ተማሪዎች በደሴ፣ ኮምቦልቻና ወልዲያ ከተማ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። በተመሳሳይ በመቀሌ እና አክሱም ለሚገኙ አንድ ሺ ሴቶች ድጋፍ ማድረጉን ያስታውሳሉ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግምታዊ ዋጋው አንድ ሚሊዮን የሚሆን የንፅህና መጠበቂያ ግብአቶችን ለሁለት ሺ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ ማድረጉን በመግለጽም፤ ድጋፉ ቀጣይነት እንደሚኖረው ጠቁመዋል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ተመድ በጋዛ የተኩስ አቁም እንዲደረግ ያቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ አሜሪካ መቃወሟን ቻይና አወገዘች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በጋዛ አስቸኳይ የተኩስ አቁም እንዲደረግ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ አሜሪካ መቃወሟን ቻይና በፅኑ አወገዘች።

ቤጂንግ ውሳኔው «የተሳሳተ መልዕክት የሚያስተላልፍ» ሲሆን በጋዛ እየተካሄደ ያለው ጭፍጨፋ እንዲቀጥል ፈቃድ የሚሰጥ ነው ብላለች።

ዋይት ሃውስ በበኩሉ በአልጀሪያ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ጦርነቱን ለማስቆም የሚደረገውን ንግግር ያደናቅፋል ብሏል።

አሜሪካ እሥራኤል ራፋህ ከተማን እንዳትወር የሚያስጠነቅቅ 'ጊዜያዊ የተኩስ አቁም' እንዲደረግ በግሏ ሃሳብ ያቀረበች ቢሆንም በጋዛ ጦርነት በቀጠለበት ወቅት አልጀሪያ ያቀረበችውን ሃሳብ መቃወሟ ሰፊ ተቃውሞ ገጥሞታል።

በጋዛ የተኩስ አቁም እንዲደረግ የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ከ15ቱ የጸጥታው ምክር ቤት አባል ሀገራት በ13ቱ የተደገፈ ሲሆን ዩናይትድ ኪንግደም ድምጿን አቅባለች።

የውሳኔ ሃሳቡ ለመጽደቅ ቢያንስ የዘጠኝ አባል ሀገራት የድጋፍ ድምጽ እንዲሁም አሜሪካን ጨምሮ የሁሉም ቋሚ የምክር ቤቱ አባላት ድጋፍ ያስፈልጋል።

የቻይና የተመድ አምባሳደር ዣንግ ጁን የአሜሪካን ውሳኔ ተከትሎ በሰጡት ምላሽ፣ ውሳኔው እየተካሄደ ላለው ዲፕሎማሲያዊ ድርድር እንቅፋት ይሆናል መባሉን «ምክንያታዊ ያልሆነ» ብለውታል።

አምባሳደሩ ጨምረውም «ጦርነቱ ወደ ሌላ አካባቢ መስፋፋቱ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ወደ ሰፊ ጦርነት እንዲገቡ ይመራል» ብለዋል።

ጦርነቱ ወደ ሌሎች የቀጣናው አካባቢ እንዳይዛመት መከላከል የሚቻለውም በጋዛ ያለውን ጦርነት በማስቆም እንደሆነ አምባሳደሩ ተናግረዋል።



የአልጀሪያ ከፍተኛ የተመድ ዲፕሎማት አማር ቤንድጃማም «በሚያሳዝን ሁኔታ የጸጥታው ምክር ቤት በድጋሜ ሳይሳካለት ቀርቷል። ታሪክ ይፋረዳችኋል፤ ህሊናችሁን ፈትሹ» ብለዋል። የአሜሪካ አጋሮችም ውሳኔዋን ተችተዋል።

የፈረንሳይ የተመድ መልዕክተኛ ኒኮላስ ዲ ሪቪየር፣ በጋዛ ያለውን አስከፊ ሁኔታ በመግለጽ የውሳኔው ሃሳብ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ማዘናቸውን ተናግረዋል።

በተመድ የዋሽንግተን አምባሳደር የሆኑት ሊንዳ ቶማስ ግሪንፊልድ በበኩላቸው በሐማስ እና በእሥራኤል መካከል ድርድር እየተካሄደ ባለበት የተኩስ አቁም እንዲደረግ ጥሪ ለማቅረብ ትክክለኛው ሰዓት አይደለም ብለዋል።

የዩኬ አቻቸው ባርባራ ውድዋርድም «ውሳኔው ድርድሩን አደጋ ላይ በመጣል የተኩስ አቁም እንዲደረግ የሚኖረውን ዕድል ይቀንሳል» ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

እሥራኤል፣ ሐማስ ባለፈው ጥቅምት ወር ላይ የሀገሪቷን ድንበር ጥሶ በመግባት ባደረሰው ድንገተኛ ጥቃት 1 ሺህ 200 ሰዎች ከተገደሉ እና ከ240 በላይ ሰዎች ታግተው ከተወሰዱ በኋላ ነበር በጋዛ ላይ ጥቃት የከፈተችው።

የእሥራኤል ጦር በጋዛ ላይ በከፈተው በዚህ ዘመቻም ከ29 ሺህ በላይ ፍልስጤማውያን መገደላቸውን በሐማስ የሚመራው የጤና ሚኒስቴር አስታውቋል።

አሜሪካ በራሷ ያቀረበችው የውሳኔ ሃሳብ፣ጊዜያዊ የተኩስ አቁም እንዲደረግና በፍጥነት ተግባራዊ እንዲሆን፣ ታጋቾች እንዲለቀቁ እንዲሁም በጋዛ እርዳታ እንዲደርስ መሰናክሎች እንዲነሱ ይጠይቃል።

አሜሪካ ያቀረበችው ሃሳብ ላይ የጸጥታው ምክር ቤት ድምጽ ስለመስጠቱ እንዲሁም መቼ ሊሰጥ እንደሚችል ግልጽ አይደለም።

ዋይት ሃውስ እሥራኤል በራፋህ ላይ ለመፈፀም ያቀደችው የምድር ጥቃት በሰላማዊ ሰዎች ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንደሚያስከትልና በተለይ ግብፅን በመጥቀስ ወደ ጎረቤት ሀገራት እንዲሰደዱ እንደሚያደርግ ገልጻለች።

ሆኖም የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤኒያሚን ኔታንያሁ ሐሙስ ዕለት ግባቸውን እስከሚያሳኩ ድረስ ጦርነቱን ለመቀጠል ቁርጠኛ መሆናቸውንና ምንም ዓይነት ግፊት ይህን አቋማቸውን እንደማይለውጠው ተናግረዋል።

ግማሽ የሚሆነው የጋዛ ሰርጥ ነዋሪዎች ማለትም ከአንድ ሚሊዮን በላይ ፍልስጤማውያን በራፋህ ተጠልለው ይገኛሉ። ከግብፅ ጋር የምትዋሰነው ደቡባዊቷ ከተማ ከጦርነቱ በፊት 250 ሺህ የሚሆኑ ሰዎች መኖሪያ ነበረች።

አብዛኞቹ ተፈናቃዮች በጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያ አሊያም በድንኳን ውስጥ ያለ በቂ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እና ምግብ ነው ተጠልለው የሚገኙት።

እሥራኤል በከተማዋ ላይ ጥቃት ለመፈፀም የያዘችው እቅድ ወደ አስከፊ ጭፍጨፋ ሊያመራ ይችላል ሲል ተመድ ቀደም ብሎ አስጠንቅቋል። የእሥራኤል ጦር በበኩሉ የሐማስ ተዋጊዎችን ብቻ ኢላማ እንደሚያደርግ ገልጿል።

የእሥራኤል ጦርነት የካቢኔ አባል ቤኒይ ጋንትዝ፣ ሐማስ ያገታቸውን እሥራኤላውያን እስከ መጋቢት 01/2016 ዓ.ም ድረስ ካልለቀቀ የምድር ጥቃቱ እንደሚከፈት አስጠንቅቀዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ለዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ዝግጅቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም አትሌቲክስ ዓመታዊ የውድድር መርሀ ግብር መሰረት የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ቻምፒዮና ከሳምንት በኋላ በስኮትላንድ አዘጋጅነት በግላስኮ ከተማ ይካሄዳል። የመም ሩጫ እና የሜዳ ተግባራት ውድድሮች ብቻ የሚስተናገዱበት የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ዘንድሮ ለ19ኛ ጊዜ የሚካሄድ ሲሆን፤ ለሶስት ቀናትም ይቆያል። በቻምፒዮናው በ29 ውድድሮች አትሌቶች ለአሸናፊነት የሚፋለሙም ይሆናል፡፡

በቻምፒዮናው በስኬታማነት ተጠቃሽ ከሆኑት የአትሌቲክስ ሀገራት አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያም እንዳለፈው ጊዜ በሜዳሊያ ሰንጠረዡ ቀዳሚ ሆና ለማጠናቀቅ ብሄራዊ ቡድኗ ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ኢትዮጵያ በየሁለት ዓመቱ በሚካሄደው ውድድር በርካታ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ከዓለም ቀዳሚ ሀገራት ጋር የምትሰለፍ ሲሆን፤ ከአፍሪካ ደግሞ የሚስተካከላት የለም፡፡ በዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና 268 ሜዳሊያዎችን በማስቆጠር ከላይ የተቀመጠችው አሜሪካ በሩጫ እና በሜዳ ተግባራት ውድድር እጅግ በርካታ አትሌቶችን ታሰልፋለች፡፡

ከዓለም የትኛውም የአትሌቲክስ ውድድር የታገደችው ሩሲያ በበኩሏ አስቀድማ በሰበሰበቻቸው ሜዳሊያዎች ቁጥር(145) በደረጃ ሰንጠረዡ በሁለተኛነት ተቀምጣለች፡፡ ሦስተኛዋ ሀገር ኢትዮጵያ ደግሞ በመድረኩ 59 ሜዳሊያዎችን አግኝታለች፡፡ ከእነዚህ መካከልም 31የወርቅ፣ 13የብር እና 15 የነሃስ ሜዳሊያዎች ናቸው፡፡

እአአ በ2022 የሰርቢያዋ ቤልግሬድ አዘጋጅ በነበረችበት 18ኛው ቻምፒዮና ደግሞ ኢትዮጵያ 4የወርቅ፣ 3 የብር እና 2የነሃስ በጥቅሉ 9 ሜዳሊያዎችን በማስቆጠር አሜሪካና ቤልጂየምን በማስከተል ከዓለም አንደኛ ሆና ማጠናቀቋ የሚታወስ ነው፡፡ ይህንንም ተከትሎ ከቀናት በኋላ ማለትም ከየካቲት22 እስከ 24/2016ዓም በሚካሄደው ውድድር ላይ ኢትዮጵያ በርካታ ሜዳሊያዎችን በማግኘት በደረጃ ሰንጠረዡ አናት ተቀምጣ ንግስናዋን ታስጠብቃለች በሚል ይጠበቃል፡፡

ይህ የሆነበት ዋነኛው ምክንያት ደግሞ ቻምፒዮናው ከመካሄዱ ሳምንታት አስቀድሞ በበርካታ የዓለም ሀገራት በሚካሄዱ የዓለም የቤት ውስጥ ቱር ውድድሮች በመካፈል በሚያስመዘግቡት አስደናቂ ስኬት ነው፡፡ በተለይ የወርቅ ደረጃ ባላቸው ውድድሮች በተለያዩ ርቀቶች ተወዳድረው አሸናፊ ከመሆን ባለፈ የቦታውን ፈጣን ሰዓት ጭምር በማሻሻል ብቃታቸውን ሲያስመሰክሩ ቆይተዋል፡፡ በዓለም አቀፉ ተቋም ወርቅ ደረጃ ከተሰጣቸው ውድድሮች የመጨረሻውም ነገ ማድሪድ ላይ ከተካሄደ በኋላ የቱር ውድድሩ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡

አትሌቶች በቱር ውድድሩ የሚያስመዘግቡት ሰዓት የቻምፒዮናውን ሚኒማ የሚያሟላ ከሆነ ሀገራቸውን የመወከል ዕድል የሚያገኙ ሲሆን፤ በተሳትፏቸው የሚያስመዘግቡት ነጥብ ተደማምሮ የተሻለ ከሆነ ደግሞ በቀጥታ ውድድሩ ላይ የሚያሳትፋቸውን የይለፍ ካርድ(wild card) ይወስዳሉ፡፡

በዚህም መሰረት የቻምፒዮናውን መስፈርት ማሟላት የቻሉ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከየካቲት 11/2016ዓ.ም አንስቶ ልምምድ ማድረግ የጀመሩ መሆኑን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መረጃ ይጠቁማል፡፡ 8 ሴቶች እና 5 ወንድ በድምሩ 13 አትሌቶችን ያቀፈው ብሄራዊ ቡድኑ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ መም ዝግጅታቸውን አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡ ቡድኑ በውድድሩ የሚካፈልባቸው ርቀቶችም በሁለቱም ጾታ 1ሺ500 ሜትር እና 3ሺ ሜትር እንዲሁም በ800 ሜትር ሴቶች መሆኑ ታውቋል፡፡



የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና ዝግጅት ቀጥሏል፤

በተለያዩ ርቀቶች የዓለም ቻምፒዮና፣ የክብረወሰን ባለቤቶችን፣ በውድድሩ ልምድ ያላቸውና ከዚህ ቀደም ውጤታማ የነበሩ እንዲሁም ወጣት አትሌቶችን ያቀፈው ቡድኑ እንዳለፈው ቻምፒዮና ውጤታማ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በቤት ውስጥ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ የምትታወቀውና በተለይም ውጤታማ የሆነችው በ1ሺ500 ሜትር ርቀቶች ሲሆን፤ የቻምፒዮናው ክብረወሰንም በሁለቱም ጾታዎች የተያዘ ነው፡፡

አስደናቂ የሆነው የ3ሺ ሜትር ወንዶች ክብረወሰን በአንጋፋው ጀግና አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ እአአ በ1997 ፓሪስ ላይ የተመዘገበው 7:34.71 የሆነ ሰዓት እስካሁን ሊሻሻል አልቻለም፡፡ በ1ሺ500 ሜትር ደግሞ ቤልግሬድ ላይ አትሌት ሳሙኤል ተፈራ የገባበት 3:32.77 የሆነ ሰዓት ነው፡፡ ቤልግሬድ ላይ በሴቶችም 1ሺ500 ሜትር በጀግናዋ አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ 3:57.19 የሆነ ክብረወሰን ተመዝግቧል፡፡